

# ትንሣኤ



ጎንደር ደብረ ኃይል በዓታ ቤተ ክርስቲያን

ቁጥር ፸፱

የካቲት ፲፱፻፸፯ ዓ.ም



የ[illegible]ት ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን

ዋጋው አንድ ብር

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ፤ሥርዓትና ዜና፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጒሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »


**አዘጋጅ**
ሊሣነወርቅ በዛብጎ ፤
ም/ ከነፈ ርግብ ማርቆስ


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

**የስልክ ቁጥር** 110754
**የመልእክት ሣ. ቁ.** 3137
**አዲስ አበባ፤**


# ማውጫ

**አርእስት** **ገጽ**


ደብዳቤዎች ........................ ፩
ስለጽድቅ የሚራቡ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ........................ ፪
የጥምቀት መታሰቢያ በዓል በደመቀ ሁኔታ ተከበረ ........................ ፬
የብፁዕ አትናቴዎስ ሥርዓተ ቀብር ........................ ፮
የነነዌ ጾም ........................ ፰
ዜና ሊቃውንት ........................ ፱
የቤተ ሰብእ ዓምድ ........................ ፲፪
ከዋሻ ውስጥ የተሠራችው የደብረ ዘመዶ ማርያም ገዳም ታሪክ.. ፲፫
በሰላም አሰናብተኝ ........................ ፲፭
የነበር ይናገር ........................ ፲፮
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........................ ፲፯
ፕሮፌሰር ሐየርና ተከታዮቻቸው ........................ ፳
የግብርና በረከት ........................ ፳፪
የጤና ዓምድ ........................ ፳፫
ኪዳነ ምሕረት ........................ ፳፬


ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ አዲስ አበባ ፤ በቅድሚያ መንፈሳዊ ሰላምታዬን አቀርባለሁ ፤ ከሰላምታዬ ቀጥዬ ደግሞ የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቀርባለሁ ።

፩ኛ/ በየሳምንቱ የምናከብራት ዕለተ እሁድ በሀገራችን ኢትዮጵያ ብቻ ነው የምትከበረው ? ወይስ በሌላው ዓለም ያሉ ክርስቲያኖች ያከብሯታል ?

፪ኛ/ በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ብዙ መጻሕፍተ ገድላት መኖራቸው ግልጽ ነው ። እነዚህን ገድላት ስናነብ የጻድቃንንና የሰማዕታትን በዓል ያከበረ በስማቸውም ዝክር የዘከረ ሰው ጻድቃን ሰማዕታት እስከተወሰነ ትውልድ ድረስ የልጅ ልጆቹን ሊያድኑለት እግዚአብሔር ቃል ኪዳን እንደሰጣቸው እንረዳለን ። ነገር ግን ልጆቹ በእግዚአብሔር የማያምኑ የአባታቸውን አርአያ የማይከተሉ ቢሆኑ አባታቸው በሠራው መልካም ሥራና በአባታቸው እምነት ሊድኑ ይችላሉን ?

፫ኛ/ በውዳሴ ማርያም ትርጉም እስመ በፈቃዱ ላይ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊት መላእክት ለተልዕኮ ወደሰማይ አይወጡም አይወርዱም ነበር ፤ ይላል ምነው ቅዱስ ሚካኤል እስራኤልን ከግብፅ ለማውጣት ከእግዚአብሔር ተልዕኮ አልነበረምን ከሎጥ ቤትስ ሁለት መላእክት ከእግዚአብሔር ተልከው መጥተው አላደሩም ወይ ?

፬ኛ/ ታዴዎስ ሐዋርያው ሰው ወደ ሚበሉት ሰዎች ሂዶ አስተማረ ይባላል ሰውን የሚበሉ ሰዎች አሉ ወይ ?

፭ኛ/ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው በእንጨት ላይ ሲሆን ቀሳውስት የብረት የናስ የብርና የወርቅ መስቀልን ለምን ይይዛሉ ?

ከ1-5 ተራ ቁጥር ላቀረብኳቸው ጥያቄዎች መልሳቸውን በትንሣኤ መጽሔት እንደምትገልጹልኝ በተስፋ እጠብቃለሁ ።

ተማሪ ሀብቱ ንጉሤ ከአላማጣ የሰንበት ት/ቤት
ወሎ ሀ/ ስብከት
ራያና ቆቦ አውራጃ

መልስ ፤

ተማሪ ሀብቱ ንጉሤ ስላቀረብክልን መንፈሳዊ ሰላምታ እያመሰገን ላቀረብካቸው ጥያቄዎች እንደሚከተለው መልስ እንሰጣለን ።

፩ኛ/ በየሳምንቱ የምናከብራት ዕለተ እሁድ በእኛ ሀገር ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም የሚገኙ ክርስቲያኖችም ያከብሯታል ።

፪ኛ/ ጻድቃን ሰማዕታት በእግዚአብሔር አምኖ የተማፀነባቸውን ክርስቲያን እስከተወሰነ ትውልድ ድረስ እንደሚያድኑ ቃል ኪዳን ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው መሆኑ የተረጋገጠ ነው ። ነገር ግን የተሰጣቸው ቃል ኪዳን ሊያድን የሚችለው በእግዚአብሔር ስም አምኖ ተጠምቆ ሃይማኖቱን አጠንክሮ ሥነ ምግባሩን አሳምሮ ለኖረ ሰው ነው እንጂ በሥጋ ተወልዶ ያላመነውንና ያልተጠመቀውን ሥነ ምግባሩ ያላማረውን ሊያድነው አይችልም ።

ይህንንም መጥምቁ ዮሐንስ "የአብርሃም ልጆች ነን በማለት የምትድኑ አይምሰላችሁ እግዚአብሔር ከእነዚህ አሕዛብ ወገን የአብርሃም ልጆችን ሊያሥነሣ ይችላል" በማለት ገልጾታል ። ማቴ. ፫ ፱ ።

በተጨማሪም እግዚአብሔር ለሙሴ በሰጠው በመጀመሪያው ትእዛዝ ላይ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና የአባቶችን ኃጢአት በልጆች የምቀጣ እስከ ሦስት እስከ አራትም ትውልድ ድረስ ለሚጠሉኝ ምሕረትንም የማደርግ እስከ ብዙ ሺህ ትውልድ ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ" ይላል ዘፀ ፳ ፤ ፭ ።

ይህም የሚያስረዳን ትእዛዙን ለሚጠብቁ በስሙ ለሚያምኑ የእግዚአብሔር ምሕረት የሚደረግላቸው መሆኑን በእርሱ ለማያምኑና ትእዛዙን ለማይጠብቁ ግን የእግዚአብሔር ምሕረት የሚከለከልባቸው ከፈጣሪም የተሰጠው ቃል ኪዳን የማይፈጸምላቸ መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ ተማሪ ሀብቱ እንደጠየቅኸው በገድለ ጻድቃንና ሰማዕታት የተሰጠውም ቃል ኪዳን ሃይማኖታውያን ወላጆቻቸውን ለሚከተሉ ይደረግላቸዋል።እንጂ የወላጆቻቸውን እምነት ሳይከተሉ ሥነ ምግባራቸውን ሳያሳምሩ ፈጣሪያቸውን ሳያውቁ ኑረው በሞቱ ጊዜ ለሃይማኖታውያን አባቶቻቸው በተሰጠው ቃል ኪዳን መሠረት መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ አይችሉም።

፫ኛ/ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከመወለዱ በፊትም ሆነ ከተወለደ በኋላ መላእክት የሰውን ጸሎትና መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር ፣ የእግዚአብሔርን ምሕረት ወደሰው ለማድረስ ተልእኳቸውን ያቋረጡበት ጊዜ የለም ። ከውዳሴ ማርያም ላይ መተርጉማን የሚናገሩትም የእመቤታችን የድንግል ማርያምን ክብር ለማጋነን ነው እንጂ መላእክት ከመላላክ ቦዝነው ተቀምጠው ነበር ለማለት አይደለም ። ቅዱስ ገብርኤል ፫ቱ ደቂቅን ከነበልባለ እሳት ያዳናቸው ዳንኤልን ከአንበሳ አፍ ያዳነው ከእግዚአብሔር ተልኮ መጥቶ ነው ። ይኸው መልአክ ወደ ድንግል ማርያም በመላክ በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ኢየሱስን እንደምትወልድ ሲያበስራት ወደ ኤልሳቤጥም በመሄድ ዮሐንስን እንደምትወልድ አብስሯታል ።

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል

## ርእሰ አንቀጽ

# "ስለጽድቅ የሚራቡ ንዑዳን ክቡራን ናቸው"

ለረኀብ ሁለት አቅጣጫዎች አሉት አንደኛው ሥጋዊ ረኀብ ሲሆን ሁለተኛው መንፈሳዊ ረኀብ ነው ። ሥጋዊ ረኀብ ደመ ነፍስ ባላቸው ፍጡራን ሁሉ የሚደርስ ነው መንፈሳዊ ረኀብ ግን ሊደርስ የሚችለው በማንኛውም ፍጡር ላይ ሳይሆን በሰው ልጆች ላይ ነው ።

የሰው ልጆች የሁለት ዓለማት ኗሪዎች ስለሆኑ በምድር ላይ ለተወሰነ ዘመን ከኖሩ በኋላ ነፍስና ሥጋቸው ሲለያዩ ዘለዓለማዊ ኑሮን ለመኖር ወደሚችሉበት መንግሥተ ሰማያት ይተላለፋሉ ። ስለዚህም በዚህ ዓለመ ሥጋ በሚኖሩበት ጊዜ ሥጋዊና መንፈሳዊ ምግቦች ያስፈልጓቸዋል ። ምግበ ሥጋ ሲያጡ ነፍሳቸው ከሥጋቸው እንደምትለይ መንፈሳዊ ምግብንም ካላገኙ ነፍሳቸው ከእግዚአብሔር አንድነት ልትለይ ትችላለች ።

ሰዎች ሥጋዊ ሕይወታቸውን በምድር ላይ ለማቆየትና ጤናማ ሕይወት ለመኖር እንደሚጥሩ ነፍሳዊ ሕይወታቸውም በክብርና በደስታ የምትኖርበትን መልካም ሥነ ምግባር የመሥራት ግዴታ ይኖርባቸዋል ። ወደ እግዚአብሔር ከሚያቀርቡትም ምግባራት አንደኛው ጾም ነው ።

በፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ ክፍል አንቀጽ ፲፭ ላይ ተጽፎ እንደሚገኘው "ጾም ሥጋ ለነባቢት ነፍስ እንድትታዘዝ የሚያደርግ መንፈሳዊ መሣሪያ ነው ። የጾምን አስፈላጊነትና ጠቃሚነት ሁሉም ሰው ያውቀዋል ። ነገር ግን ሥነ ሥርዓቱ በሁሉም ዘንድ የተለያየ በመሆኑ አንዱ ጊዜ ለይቶ ሰዓት ወስኖ ሲጾም ሌላው ደግሞ በተመቸው ጊዜ ይጾማል ። ያም ሆነ ይህ ስለጽድቅ ብሎ መራብና መጠማት ከፍተኛ ዋጋን ከእግዚአብሔር የሚያሰጥ መሆኑ አይጠረጠርም ።

ይህንንም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያስተምር "ብፁዓን እለ ይርኅቡ ወይጸምኡ በእንተ ጽድቅ" አብዝተን ከተመገብን ሰውነታችን ከኃጢአት ወስኖ ገትቶ መኖር እንደምን ይቻለናል ብለው ከሚበሉትና ከሚጠጡት እየከፈሉ ለችግረኞች በመስጠት የሚራቡና የሚጠሙ ንዑዳን ክቡራን ናቸው ብሏል ። ማቴ ፭.፮ ።

በቀድሞ ዘመን በሕንድ ሀገር በረኃብ መሞት የተቀደሰ ሞት ነው ተብሎ በአንዳንድ ሕንዳውያን ዘንድ ይታመንበት ነበር ፤ ከዚህም የተነሣ ንጉሡ አስረያማና እቴጌይቱ ትረዛላ የተባሉት ሰዎች በጣም ሃይማኖታውያን ነን ለማለት የሚበሉት እህል የሚጠጡት ውሀ ሳያጡ ሰውነታቸውን በማስራብ ሕይወተ ሥጋቸውን ያሳለፉ መሆናቸው በታሪክ ተጽፏል ። ታ.ሃ.እ. ገጽ ፳፮ ።

ነገር ግን ረኃብ ዋጋ ሊያሰጥ የሚችለው ከሚበሉትና ከሚጠጡት እየከፈሉ ለድሆች እየሰጡ የተራቡ እንደሆነ ነው ነቢዩ ዳዊት "ለችግረኞች የሚያስብ ምስጉን ነው እግዚአብሔር በክፉ ቀን ያድነዋል ፤ እግዚአብሔር ይጠብቀዋል ፤ ሕያውም ያደርገዋል ። በምድርም ላይ የተመሰገነ ይሆናል" ይላል መዝ. ፵፩.፩ ።

ችግረኞችን በሚችሉት ነገር ሁሉ መርዳት ክብርን የሚያሰጠው በነፍስ ብቻ አይደለም በዚህ ዓለምም ቢሆን ከመከራ ሥጋ የሚያድን መሆኑ አያጠራጥርም ። ራኡል ፎልሮ የሚባል አንድ ሰው በዚህ ዓለም ላይ በልዩ ልዩ ችግር ተይዘው ስለሚሠቃዩት ድሆችና በሽተኞች በሰፊው ተናግሯል ። "የእውነተኛ ፍቅር መጽሐፍ" በሚለው መጽሐፍ ውስጥ ስለ ድሆች አስቡ በሚለው ርእስ ተነሥቶ "ማልቀስና ማዘን በቀላሉ የሚደረጉ ስለሆኑ ዋጋ የላቸውም ። የሚበጀው የሰዎችን ችግር ተረድታችሁ እንዳይቀጥል መታገል ነው ። ስለራሳችሁና ስለዘመዶቻችሁ ብቻ መሥራትና በመንግሥተ ሰማያትም ለራሳችሁ ብቻ ቦታ ማዘጋጀት አይገባችሁም ። ደግ ሰው መልካሙን የሚያደርግ እንጂ ክፉ አታድርግ የሚል ብቻ አይደለም ። ሌሎች በመከራ ሲኖሩ እናንተ በድሎት መኖርን አትፈልጉ ፤ በዓለም ላይ ችግር መብዛቱን አይታችሁ ይህን ችግር ማስወገድ አይቻልም ሳትሉ ችግሩን በርትታችሁ ተዋጉት ፤ ከሁሉም አስከፊ የሆነው ነገር ግን ሕይወታችሁን ዓላማ ቢስ ስታደርጉና ምንም መልካም ሥራ ሳትሠሩ ስትቀሩ ነው" ይላል ።



በተለይ በጾም ወራት ከሌላው ጊዜ በበለጠ ለችግረኞች የምንለግሰውን እርዳታ ከፍ ልናደርግ ይገባናል ጾም የትሩፋት ሁሉ መሠረት ነውና እንድንታገሥ ለችግረኞች እንድናዝንና እንድንራራ መንፈሳዊ ኃይልን ከእግዚአብሔር ለማግኘት የምንችለው ስንጾምና ስንጸልይ መሆኑ የተረጋገጠ ነው ።

የጾም ጠቃሚነቱ በዘመነ ብሉይም ሆነ በዘመነ ሐዲስ በጉልህ ስለታወቀ ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ጊዜና ሰዓት ወስና እንዲጾሙ ለክርስቲያኖች የምታስተምራቸው ሰባት አጽማት አሏት ከእነርሱም ዋነኛው ዓቢይ ጾም ስለሆነና ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም የጾመው በመሆኑ ታላቅ የሚለው ቅጥል ተሰጥቶታል፤

አጿማቱ የሚጾሙት ከእህልና ከውሀ በመከልከል ብቻ ሳይሆን ከጸብ ከክርክር ከሐሜትና ከተንኮል ከክፋትና ከምቀኝነት ከመሳሰሉትም ተከልክሎ ለችግረኞች በመስጠት የተጣሉትን በማስታረቅ ፤ የተበደሉትን በማስካስ የተቀሙትን በማስመለስ ፍቅርንና ርኅራኄን በተሞላ ሰውነት መጾም እንደሚገባ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ታስተምራለች ።

"ኃዘንን የቀመሰ ኃዘንን ያውቃል" እንደሚባለው የሚጾም ሰው ለተራቡት ለተጠሙት ለታረዙት ሊያዝንና ሊራራ ሲችል የማይጾም ሰው ግን ረኃብን ችግርን በቀላሉ ሊረዳ አይችልም እርሱ እንደሚበላና እንደሚመገብ ሌላውም የሚመገብ ይመስለዋል ። ችግር በሰዎች ላይ ያለ አይመስለውም ።

ከዚህ ላይ አንድ ታሪክ እንመልከት ሰሎሞን የዳዊት ልጅ ነው ። አባቱ ንጉሥ ስለነበረ በቤተ መንግሥት ተወልዶ በድልድል በቅምጥል አደገ ። ፲፪ ዓመት ሲሆነውም በአባቱ በዳዊት ዙፋን ላይ ነገሠ ። አባቱም ዳዊት ጥቂት ጊዜ ቆይቶ ሞተ ። ከዕለታት አንድ ቀን አንድ ችግረኛ ስመ እግዚአብሔር እየጠራ ሲለምን ተመልክቶ ይህ ሰው ምንድን ሆኖ ነው ? ብሎ አሽከሮቹን ጠየቀ ። ርቦት ጠምቶት ምግብ እየለመነ ነው ፤ አሉት ሰሎሞንም ችግርንና ረኀብን የማያውቅ ስለነበር ረኃብ ምንድን ነው? ሲል የማይገባ ቃልን ስለተናገረ እግዚአብሔር ተቀየመው ።

ወዲያው ወደ ውጭ ሲወጣ ስመ እግዚአብሔር የተቀረጸባትን ቀለበቱን ከዙፋኑ ላይ ረስቷት ስለሄደ አሽከሮቹ ተቀምጦበት የነበረውን ምንጣፍ ከውጭ አውጥተው ሲያራግፉ ቀለበቱም ከጥራጊው ጋር ተጠርጋ ተጣለች ። ከሰሎሞንም ዙፋን ላይ ሰይጣን ተሸፋፍኖ ተቀመጠበት ። ሰሎሞን ወደዙፋኑ እገባለሁ ሲል የገዛ አሽከሮቹ ከለከሉት እኔ ሰሎሞን ነኝ እኮ ቢላቸው ሰሎሞን ከዙፋን ላይ ተቀምጧል ሁለተኛ ሰሎሞን አናውቅም ተመለስ ብለው አባረሩት ።

ሰሎሞን የሚበላውና የሚጠጣው አጥቶ በጣም ተቸገረ መንደር ሂዶ ቢለምንም ሰይጣን የሰውን ልብ ስላስጨከነበት የሚዘከረው አላገኘም አጣ ረኃብ ምንድነው ብሎ በመናገር ፈጣሪውን ስላስቀየመ በገዛ ሀገሩ በገዛ ከተማው ቁራሽ እንጀራ አጥቶ ተንከራተተ ዞረ ፤ በከተማው አቅራቢያ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና ወደእነርሱ ሂዶ ለመነ ። እንደአጋጣሚ ከጥራጊው ጋር የተጣለውን ቀለበቱን አንድ ዓሣ ውጦት ስለሞተ ሰሎሞን በለመነ ጊዜ አሣ አጥማጆቹ ያንን የሞተ ዓሣ ወረወሩለት እርሱም እርቦት ስለነበረ የዓሣውን ሆድ ዕቃ አውጥቼ እበላለሁ ሲል ቀለበቱን አገኛት ። ቀለበቱን ከጣቱ ባስገባት ጊዜ ንጉሥ ከዚህ ምን ሊያደርጉ መጡ በማለት ሕዝቡ ዙሪያውን ከቦ እያጀበው ወደ ቤተ መንግሥቱ አገባው በሰሎሞን ዘፋን ተቀምጦ የነበረውንም ሰይጣን ስመ እግዚአብሔር በመጥራት ድራሹን አጥፍቶታል ።

ሰሎሞን በገዛ ከተማው የሚበላውና የሚጠጣው አጥቶ የተንከራተተው ለተራብ ባለማዘኑና ረኃብ በሰው ላይ የሚያደርሰውን ችግር ባለመረዳት በተናገረው የማይገባ ቃል ነው ።

በሁላችንም አፍ ክፉ ነገር እንዳይወጣ መጠበቅና መጠንቀቅ ይኖርብናል ዳዊት "በምላሲ እንዳልስት መንገዴን እጠብቃለሁ አልሁ ፤ ኃጢአተኛ በፊቴ ሳለ አፌን በልጓም እጠብቃለሁ" ይላል መዝ. ፴፱. ፩

አፍን ከሐሜትና ከስድብ ከልክሎ ለምስጋና ለጸሎት ማዋል ከጾመ መባልዕት ያላነሰ ዓቢይ ቁም ነገር ነው ። ስለዚህ በክርስቶስ ክርስቲያን ተብለን የምንጠራ ሰዎች ሁሉ ዲያብሎስን የምናሸንፍበት የመንፈስ መሣሪያችን ጾም መሆኑን ተገንዝበን በፍቅርና በትሕትና ሆነን መጾም ይገባናል ። ስለጽድቅ መራብ ፤ ስለጽድቅ መጠማት ክብር የክብር ክብርን ያጐናጽፋልና ።



www.ethiopianorthodox.org

# የጥምቀት መታሰቢያ በዓል በደመቀሁኔታ ተከበረ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእደ ዮሐንስ በፈለገ ዮርዳኖስ በመጠመቅ የዕዳደብዳቢያችን የደመሰሰበት የጥምቀት መታሰቢያ በዓል የተከበረው ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ነው።

ከበዓሉ ዋዜማ ጀምሮ እስከ በዓሉ ፍጻሜ ድረስ እጅግ በጣም በደመቀ ሁኔታ የተከበረ መሆኑን ከየአህጉረ ስብከቱ የደረሰው ዜና አረጋግጧል ።

አዲስ አበባ ፤

በተለይ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ በሆነችው አዲስ አበባ ጥር ፲ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም የከተራና የጥምቀት በዓል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ፡ ካህናት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን በተገኙበት በሚያስደንቅና በሚያስደስት አኳኋን ተከብሯል ።

ጥር ፲ ቀን ከሰዓት በኋላ በ፰ ሰዓት ታቦታቱ ከየመንበረ ክብራቸው ወጥተው በካህናትና በብዙ መቶ ሺህ በሚቆጠሩ ምዕመናን ታጅበው ለማደሪያ ወደተዘጋጀላቸው ስፍራ ጉዟቸውን ቀጥለዋል ። አሥር ተኩል ሲሆን ለማደሪያ ከተዘጋጀላቸው ቦታ ጃንሜዳ ሲደርሱ "ወረደ ወልድ" የሚለው ሰላም በባለተረኞቹ የቀጨኔ ደብረ ሰላም መዘምራን ተመርቶ በሕብረት ከተዘመመ በኋላ ተለዝቦና ተሸብሽቦ ሲያበቃ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጸሎተ ቡራኬ አድርገው ታቦታቱ ወደ ተዘጋጀላቸው ድንኳን ሲገቡ የዕለቱ መርሐ ግብር ተጠቃሏል ።

ከምሽቱ በሦስት ሰዓት ካህናቱ ከዚያው በመገኘት የተለመደውን ስብሐተ እግዚአብሔር አድርሰዋል ጸሎተ ቅዳሴውም እንደተለመደው በመንፈቀ ሌሊት ተከናውኖአል ። ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም በሁለት ሰዓት ተኩል ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ካህናትና በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን በተገኙበት ጸሎት ከተጸለየ በኋላ ለጌታችን ጥምቀት መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የተጠራቀመውን ውሀ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ባርከው ከረጩ በኋላ ጸሎተ ቡራኬ በማድረግ አሳርገዋል ። ወዲያው ታቦታቱ ከድንኳኑ ተነሥተው በምእመናን ታጅበው በመዝሙር በልልታና በሆታ ወደ የቤተ ክርስቲያናቸው ጉዟቸውን ቀጥለዋል ።

ከዚያ ቀደም ሲል የቅዱስ ፓትርያርኩ ረዳት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ በዓሉን አስመልክተው መንፈሳዊ መልእክትን አስተላልፈዋል ። እንዲሁም ከስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የተወከሉ ልዑካን ከበዓሉ ዋዜማ ጀምረው እስከ ፍጻሜው ድረስ ትምህርተ ወንጌል አስተላልፈዋል ።

## አሰላ

በአርሲ ሀገረ ስብከት በአሰላ ከተማ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የአራት አድባራት ካህናት በብዙ መቶ ሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን በተገኙበት የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ጥምቀት መታሰቢያ እጅግ በጣም በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል ።

ከበዓሉ ዋዜማ ጀምሮ እስከ በዓሉ ፍጻሜ ድረስ ካህናቱ ለበዓለ ጥምቀት ማክበሪያ ከተዘጋጀው ስፍራ ተገኝተው የተለመደውን ስብሐተ እግዚአብሔር ሲያደርሱ ከጠ/ቤተ ክህነት የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የተላኩት ልኡካን

፩ኛ/ ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ

፪ኛ/ ሊቀ ትጉሃን ገብረ ክርስቶስ ኃይለ ማርያም በዓሉን ለማክበር ለተሰበሰበው ሕዝበ ክርስቲያን የዕለቱን በዓል የሚመለከት ትምህርተ ወንጌል አስተላልፈዋል ።

ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የአርሲ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ ለጌታችን ለመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት መታሰቢያ የተጠራቀመውን ውሀ ሲባርኩ ባስተላለፉት መንፈሳዊ መልእክት "በዓሉ ሃይማኖታዊና ባሕላዊ በመሆኑ ማነኛውንም ምእመን ሊያስመካውና ሊያኮራው ይችላል ብለዋል ፡ ብፁዕነታቸው ንግግራቸውን በመቀጠል መጥምቁ ዮሐንስ በሚያስተምርበት ጊዜ ጣዖት አምላኪዎችና ተንኮለኞች ለመማር ሳይሆን ለተንኮል ወደ ጉባኤው ሲመጡ ተመልክቶ እናንተ የምድር እፉኝት ልጆች ከተቃጣባችሁ መዓት ትድኑ ዘንድ ማን አስተማራችሁ ? ግንዱን ከቅርንጫፍ ለመለየት መጥረቢያ እንደሚቃጣ እናንተንም በሞት ከዚህ ዓለም ለይቶ ወደገሃነም ለመጣል ሥልጣን እግዚአብሔር ተቃጥቷልና ከዚህ ጥፋት ለመዳን እንድትችሉ ንስሐ ግቡ ብሎ ስለአስተማራቸው ወደ እርሱ መጥተው ጥያቄዎችን አቅርበውለታል ።

ሕዝቡ ምን እናድርግ ? ቢሉት ሁለት ልብስ ያለው ለሌለው ያካፍል ፡ ምግብም ያለው እንዲሁ ያድርግ ይል ነበር፡ ቀራጮችም ደግሞ ሊጠመቁ መጥተው መምህር ሆይ? ምን እናድርግ ? አሉት እርሱም ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ አላቸው ጭፍሮችም ደግሞ እኛስ ምን እናድርግ ብለው ቢጠይቁት በማንም ግፍ አትሥሩ ማንንም በሐሠት አትክሰሱ ደመወዛችሁ ይብቃችሁ ብላቸዋል ካሉ በኋላ ፡

ብፁዕ አቡነ ናትናኤል ንግግራቸውን በማራዘም የዮሐንስን ትምህርት እስከ ዛሬ ተምረነዋል ፡ ዛሬ የተማርነውን በሥራ የምንተረጉምበት ወቅት ነው በአሁኑ ጊዜ የሀገራችን ችግር ከእኛ አልፎ ዓለሙን እያሳሰበው ነው ዛሬ ዓለሙ ሁሉ ሀገራችንን ለመርዳት በመረባረብ ላይ ይገኛል እኛም በተቻለን መጠን የተቸገሩትን ወገኖቻችንን ለመርዳት እጃችን መዘርጋት ይገባናል ፡ እስከ ዛሬ ድረስ የምንጠይቃችሁ ያረጀውን ቤተ ክርስቲያን አሳድሱ ፡ የተጀመረውን አስጨርሱ ፡ የፈረሰውን አስጠግኑ እያልን ነበር ።

አሁን ግን የምንጠይቃችሁ የክርስቶስ ሕንፃ የሆኑትን ምእመናን ከረኃብና ከጽምዕ እንድታድኑ ነው በማለት ሕዝበ ክርስቲያኑ ሁሉ የተቸገሩትን ወገኖቻችን ለመርዳት እንዲተባበር አሳስበው ጸሎት አድርገዋል ፡ ወዲያው ታቦታቱ ከድንኳኑ ተነሥተው ለመሄድ ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት "ዮም ፍሥሐ ኮነ በእንተ ልደቱ ለክርስቶስ ወበእንተ ጥምቀቱ" የሚለው ሰላም ተቃኝቶ ከተዘመመ በኋላ ለዙብ ተለዝቦ ለጽ ደቂቃ ያህል ተሸብሽቧል ። ከዚያ በኋላ የደብረ ሰላም ቅዱስ ሚካኤል ታቦት ከዚያው ሲቀር ታቦተ መድኃኔዓለም ታቦተ ማርያም ታቦተ ገብርኤል ወደ የአብያተ ክርስቲያናቸው ጉዟቸውን ቀጥለዋል ።

ካህናቱ በዝማሬ የሰንበት ት/ቤት ተማሮች በመዝሙር ምእመናኑ በልልታና በሆታ ታቦታቱን አጅበው ሲጓዙ ለተመለከታቸው እጅግ በጣም የሚያስደስትና የሚያስደንቅ ነበር ።

በበነጋው ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም በዚሁ አሰላ ከተማ ብዙ ሕዝበ ክርስቲያን ተገኝቶ የቅዱስ ሚካኤልን በዓል አክብሯል ። ጸሎተ ቅዳሴው ከንጋቱ ፲፪ ሰዓት ላይ ተጀምሮ በሁለት ሰዓት ተኩል እንደተፈጸመ ከስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የተላኩት ልዑካን በዓሉን አስመልክተው በየተራ ትምህርት ሰጥተዋል ።

አራት ሰዓት ከሠላሳ ደቂቃ ሲሆን ታቦቱ ካደረበት ድንኳን ተነሥቶ በብዙ ምእመናን በመታጀብ ወደ ቤተ ክርስቲያኑ ጉዞ ሲጀምር ከጠ/ቤተ ክህነት ስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ የተላኩት ሰባክያን ቀደም ብለው ሄደው ከቤተ ክርስቲያኑ በመድረስ ታቦቱን ለመቀበል ለሚጠባበቀው ሕዝበ ክርስቲያን ትምህርተ ወንጌል ሲያስተምሩ ቆይተዋል ።

ታቦቱ ከቤተ ክርስቲያኑ ደርሶ ቤተ ክርስቲያኑን አንድ ጊዜ ዙሮ በአውደ ምሕረቱ ላይ እንደቆመ ብፁዕ አቡነ ናትናኤል የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ "በዓሉ የቅዱስ ጋብቻ በዓል ነው" በሚል ርእስ ተነሥተው ማነኛውም ሰው አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት ይብቃ የተባለውን ቃል ተከትሎ በሕግ ተወስኖ ቢኖር ለሀገር ለወገን የሚጠቅም ዘርን ተክቶ ለማለፍ ከመቻሉም ሌላ በፈጣሪውም ዘንድ ክብርን ያገኛል ካሉ በኋላ ስለጋብቻ ክቡርነት በሰፊው አስረድተው ጸሎተ ቡራኬ በማድረግ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኗል ።

## ጅማ

በየዓመቱ የሚከበረው የጥምቀት በዓል ዘንድሮም ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም በጅማ ከተማ በሚያስደስት ሁኔታ ተከብሮ የዋለ መሆኑን የደረሰው ዜና አረጋግጧል ። ጥር ፲ ቀን ከሰዓት በኋላ በጅማ ከተማ የሚገኙት የአምስት አድባራት ታቦታት ወጥተው ለበዓለ ጥምቀቱ ማክበሪያ ወደተዘጋጀው ቦታ ሲያመሩ ካህናቱ በዝማሬ ምእመናኑ በልልታና በሆታ የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች በመዝሙር ግራና ቀኝ አጅበዋቸው ይጓዙ ነበር ። ታቦታቱ ከማደሪያቸው ቦታ እንደደረሱ ሰላሙ ከተጸፉ በኋላ ከስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ በተላኩት ሊቀ መዘምራን ተሰማ ገ/ሚካኤል ትምህርት ተሰጥቷል ።

እንዲሁም ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ከሌሊቱ በ፯ ሰዓት ጸሎተ ቅዳሴው ተጀምሮ በስምንት ተኩል እንዳበቃ በዓሉን የሚመለከት ትምህርተ ወንጌል ቀላል ፏል ከቀኑ ሁለት ሰዓት ላይ የባህረ ጥምቀቱ ሥርዓተ ጸሎት ተጀምሮ እንደተፈጸመ ታቦታቱ ካደሩበት ስፍራ ተነሥተው ወደ የቤተመቅደሶቻቸው ሲጓዙ ታቦታቱን አጅቦ ይጓዝ የነበረው ሕዝብ እጅግ ብዙ ነበር ።

በተጨማሪም ከጅማ ከተማ አምስት ኪሎ ሜትር ያህል ራቅ ብሎ በሚገኘው ሸዋ በር ቅዱስ ሚካኤል ጥር ፲፪ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም የቅዱስ ሚካኤል በዓል በደመቀ ሁኔታ ተከብሮ ውሏል ። በበዓሉም ላይ ከላይ ስማቸው የተጠቀሰው ከስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ የተላኩት ሰባኪ በዓሉን የሚመለከት መንፈሳዊ መልእክት ያስተላለፉ መሆናቸውን የደረሰን ዜና አረጋግጧል ።

የዜናው አቅራቢ

ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ





www.ethiopianorthodox.org

# የብፁዕ አቡነ እእናቴዎስ ሥርዓተ ሢመት

የብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ጳጳስ የኤጲስ ቆጶስነት ሥርዓተ ሢመት ኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ·ም እሑድ በመንመረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ቤተ ክርስቲያን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ አንብሮተ እድ ተፈጽሟል ።

በስነ ሥርዓቱም ላይ ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የመምሪያ ኃላፊዎች የአድባራት አስተዳዳሪዎችና የገዳማት አበምኔቶች እንዲሁም አያሌ ካህናትና ምእመናን ተገኝተዋል ።

ስለ ሥርዓተ ሢመቱ አፈጻጸም በወጣው መርሐ ግብር መሠረት ቅዳሜ ኅዳር ፰ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም ከቀትር በላይ የጸሎተ አስኬማው ሥርዓት በተለመደው ሁኔታ የተከናወነ ሲሆን በማግሥቱ ኅዳር ፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም እሁድ የኤጲስ ቆጶስነቱ ሥርዓተ ሢመት በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ አንብሮተ እድና ጸሎት ቡራኬ ተፈጽሟል ።

በዚሁ ዕለት ቀደም ሲል ከሌሊቱ በ፲፩ ሰዓት ጀምሮ የሥርዓተ ሢመቱ ጸሎት በብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ መሪነት በብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የተካሄደ ሲሆን የጸሎተ ቅዳሴውም ሥርዓት የተፈጸመው በቅዱስነታቸው መሪነት ነው በዚህም ወቅት ተሿሚው ኤጲስ ቆጶስ ቃለ መሐላቸውን ፈጽመዋል ።

በሥርዓተ ሢመቱም ወቅት ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ በጎቼን ጠብቅ "ከ ሚለው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንባብ በመነሣት የኤጲስ ቆጶስነት ሹመት ለመዝናናትና ለደስታ ሳይሆን በበጎች የተመሰሉ ምእመናንን በትምህርተ ሃይማኖት ለመጠበቅ መሆኑን ጠቅሰው ይህን ሐዋርያዊ ተግባር በሚገባ ለማከናወንና መንፈሳዊ ኃላፊነትን ለመወጣት ቀደም ካለው ጊዜ ይልቅ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ትግልና ፈተና እንዳለ አስረድተዋል ።

እንዲሁም በኢየሩሳሌም ያሉትን የኢትዮጵያን ገዳማት በመጠበቅና በማስጠበቅ በዚያ የሚገኙትንም መናንያን በመንከባከብና ቅድስት ሀገርን ለመሳም ከኢትዮጵያና ከዓለም ዙሪያ የሚሄዱትን የሀገር ጎብኚዎች በማስተናገድ (በመቀበል) ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ በማድረጋቸው ለዚህ መንፈሳዊ ክብር መብቃታቸውን በማውሳት ወደፊትም በተጣለባቸው ኃላፊነት ለገዳሙም ሆነ በጠቅላላው ለቤተ ክርስቲያናቸው ከፍተኛ ውጤት እንደሚያሳዩ ካስገነዘቡ በኋላ ጸሎተ ቡራኬ ሰጥተው ጠቅላላ የበዓለ ሢመቱ ፍጻሜ ሆኖአል ።

በዚሁ ዕለት ስለ በዓለ ሢመቱ ክብር ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርክ የምሳ ግብዣ አድርገዋል ። በግብዣውም ላይ ብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ ባደረጉት ንግግር "ጀግና ከጦር ሜዳ ይወለዳል" እንደሚባለው ሁሉ በኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ ገዳማት ታሪካዊ ይዞታ ብዙ የታገሉትና የደከሙት ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ መሾማቸው ትክክለኛ ፍትሕ መሆኑን አመልክተው በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተወካይ ጳጳስ መኖር ክብሩ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን መላውን የጥቁር ዓለም የሚያስመካ መሆኑን በማውሳት ወደፊትም በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያን ገዳማት ታሪካዊ ይዞት ለማስፋፋትና የራስን ድክመቶች ለማስወገድ አዲሱን ጳጳስ ብዙ ድካምና ጥረት እንደሚጠብቃቸው አሳስበዋል ።

ቀጥሎም ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ባደረጉት ንግግር በውስጥም ሆነ በውጭ የደረሰባቸውን ፈተና በትዕግሥት ተቋቁመው በኢየሩሳሌም ለኢትዮጵያ ገዳማት ብዙ የታገሉትና ልዩ ልዩ ምግባር ትሩፋት የፈጸሙት ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ለጵጵስና ክብር እንዲበቁ በማድረጉ (በመወሰኑ) ቅዱስ ሲኖዶስን አመስግነው የቤተ ክርስቲያንን ብቃትና ጥረት እንደሚጠይቅ ገልጸዋል።

በተጠቀሰው ዕለት ምሽት የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ስለበዓለ ሢመቱ ክብር ለብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት የራት ግብዣ አድርጓል ። በዚሁ ወቅት አቶ መኮንን ዘውዴ የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ በአሁኑ ወቅት ብዙ መዝናናት አስፈላጊ ሆኖ ሳይሆን የራት ግብዣው የተደረገበት ምክንያት ለበዓለ ሢመቱና ለቅድስት ሀገር ለኢየሩሳሌም ክብር ሲባል መሆኑን ጠቅሰው የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ከተቋቋመበት ከ፲፱፻፶፭ ዓ.ም ጀምሮ እንደታዘበው ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ለገዳሙ አያሌ ተጋድሎ ያደረጉ በመሆናቸው ቅዱስ ሲኖዶስ ለዚህ መዐርግ እንዲበቁ በማድረጉ ድርጅቱ ከፍ ያለ ደስታ የተሰማው መሆኑን በመግለጽ አብዮታዊው መንግሥትና ቤተ ክህነት ለኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅትም ሆነ ለገዳማቱ የሚያደርጉትን ርዳታና ድጋፍ ካመሰገኑ በኋላ አሁንም በገዳማቱ ገና የሚቀር ችግር ስለአለ በብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ ጥረትና በሚመለከታቸው አካላት ትብብር ችግሩ ሊቃለል እንደሚችል አመልክተዋል ።

በመጨረሻም የባሌ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ሰላማ ባደረጉት ንግግር ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ በኢየሩሳሌም የፈጸሙትን ተጋድሎና ያከናወኑትን ታላቅ ተግባር በመጥቀስ ሥራ ሠሪውን ስለሚፈልግ ወርቅ በእሳት እንደሚፈተን ሁሉ በመከራ የተፈተነ ስውነታቸው ለዚህ መንፈሳዊ ክብር እንዲበቃ መደረጉ ተገቢ መሆኑን ገልጸው የኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት የሚያደርገውን የተቀደሰ ትብብር በማመስገን ጸሎተ ቡራኬ አድርገዋል ።



የብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ የሕይወት ታሪክ ባጭሩ

ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ በወሎ ክፍለ ሀገር በዋድላ ደላንታ አውራጃ በዳውንት ወረዳ በደገላ ማርያም ከአባታቸው ከብላታ ገረመው ጎባውና ከእናታቸው ከ/ወ/ሮ እታገኝ ግኔው በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም ተወለዱ ።

ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ ዳውንት ውስጥ የሳይ ጊዮርጊስ ከሚባለው ቦታ ከመ/ፈታሒ ቢምር ዳዊት ጾመ ድጓና የዘወትር ምዕራፍ ተማሩ ከዚያም ወደ በጌምድር ሄደው ከአለቃ ገብረሐና አገር ፎገራ አውራጃ ናቢጋ ጊዮርጊስ ከሚባለው ሥፍራ ከመ/ገብሩ ድጓና ጾም ምዕራፍ ተምረዋል ።

ቀጥሎም ጎንደር ውስጥ ከመ/ከሃሊ ዓለሙ አቋቋምና ዝማሬ መዋሥዕት ተማሩ ከዚያም በዚሁ በጎንደር ከምከም ቃሮዳ ከሚባለው ቦታ ብርኩቱ ማርያም ከምትባለው ደብር ከመምህር ገብረ ሕይወት ቅኔ ከነአገባቡ ተማሩ ከዚህ በኋላ ወደ ጎጃም ሄደው ሜጫ ከሚባለው ሥፍራ ከመ/ መንክር ብርሌ ለመምህርነት በሚያበቃ ደረጃ የድጓ ትምህርት ተማሩ ከዚያም እንደገና ወደ ጎንደር ተመልሰው ግምጃ ቤት ማርያም ከታወቁት የሐዲስ መምህር ከመምህር ክፍሌ ትርጓሜ ሐዲስ አጠኑ ።

ከዚህ በኋላ በ፲፱፻፵፫ ዓ/ም ወደ አዲስ አበባ መጥተው በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፈቃድና ትእዛዝ በማኅበረ ዊ ኑሮ ከሚያገለግሉት መነኮሳት አንዱ አገልጋይ ሆነው ተመደቡ በ፲፱፻፵፰ ዓ/ም የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ አቡነ ቀሲስ ሆነው ተሾሙ በ፲፱፻፶፫ ዓ ም ብፁዕ አቡነ ዮሴፍ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት አስተዳዳሪ ሆነው ሲሄዱ የብፁዕነታቸው ረዳትና አማካሪ ሆነው ሄዱ ።

በዚሁ ሥራ ላይ እንዳሉ በ፲፱፻፷፩ዓ.ም ከገዳሙ ምክር ቤት ዓባላት አንዱ ሆኑ በዚሁ ዓ/ም በኢየሩሳሌም የደብረ



ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ

ገነት ኪዳነ ምሕረት ገዳም ቄስ ገበዝ ሆኑ በ፲፱፻፷፭ ዓ/ም መጋቢ ገነት በመባል የዚሁ ገዳም አበምኔት ሆነው ተሾሙ በ፲፱፻፷፰ ዓ/ም ለከፍተኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የፖትርያርክነት ምርጫ ከተወዳደሩት አምስት አበው አንዱ ሆነው በመቅረብ ተወዳደሩ ከ፲፱፻፸-፲፱፻፸፩ ዓ/ም ጠቅላላ ገዳሙን በመጋቢነት መሩ (አስተዳደሩ) ።

ብፁዕ አቡነ አትናቴዎስ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ገዳማት ት/ቤት በማቋቋምና መዘክሮችን በመሰብሰብ ስለገዳማቱ አቋምና ይዞት ከግብጾችና ከሚመለከታቸው የእስራኤል መንግሥት ባለሥልጣኖች ጋር ሰፊ ትግል በማድረግና ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በመወያየት አያሌ ጉዳዮች በሰላም እንዲፈጸሙ ከማድረጋቸውም በላይ የገዳማቱን ማኅበራዊ አንድነት በማጠናከርና የሚተዳደሩበት መመሪያ በማውጣት አብያተ ክርስቲያናትን በማሳደስ በገዳሙ ት/ቤት በዕብራይስጥ ቋንቋ በማስተማርና በኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት ሥር ያሉትን ምዕመናንና ሌሎችንም የሀገር ጎብኝዎች በማስተባበርና በኢየሩሳሌም ላሉት የኢትዮጵያ ገዳማትና መናንያን ከሃያ ዓመት በላይ ቀና አገልግሎት ያበረከቱና ሐዋርያዊ ተልእኮአቸውን የፈጸሙ አባት ስለሆኑ ሁሉም እንደሳቸው በሥራ ቢመረጥ መልካም ነው ።

ብፁዕነታቸው በሥርዓተ ሢመቱ ላይ የፈጸሙትን ቃለ መሐላም ከዚህ እንደሚከተለው አቅርበነዋል ።

የብፁዕነታቸው ቃለ መሐላ

እኔ አባ ዮሐንስ ከሃሊ በኔሬይቱ ዕለት በእግዚአብሔር ፈቃድ የቤተ ክርስቲያናችንን ከፍተኛ ማዕረግ የኤጲስ ቆጶስነትን ሥልጣን ለመቀበል ስቀርብ ከዚህ እንደሚከተለው የእምነቴን ቀኖና ለቤተ ክርስቲያን እገልጣለሁ ።

፩ኛ/ ከሁሉ በፊት በ፫፻፳፭ ዓ/ም በኒቅያ የተረቀቀውንና በሠለስቱ ምዕት የጸደቀውን የሃይማኖት ቀኖና እቀበላለሁ።

፪ኛ/ በ፫፻፹፩ ዓ/ም በቁስጥንጥንያ የተወሰነውንና በ፬፻፴፩ ዓ/ም በኤፌሶን የተወሰነውን ውሳኔ ባጠቃላይ የሦስቱንም ጉባኤያት ውሳኔዎች እስከ ሕይወቴ ፍጻሜ አክብሬ እጠብቃለሁ ፡ አስጠብቃለሁ ።

፫ኛ/ በ፬፻፶፩ ዓ/ም በኬልቄዶን የተደረገውን ጉባኤ እንደ ሃይማኖት አባቴ እንደ ቅዱስ ዲዮስቆሮስ እወግዛለሁ ።

፬ኛ/ ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ አካል አንድ ባሕርይ መሆኑን አምናለሁ ።

፭ኛ/ ኢየሱስ ክርስቶስ በአንድ ግብር በአንድ ፈቃድ የማዳን ሥራውን እንደሚሠራ አምናለሁ ።



www.ethiopianorthodox.org

# የነነዌ ጾም

ነነዌ የምትባለው ሀገር ከእሥራኤል ሊባኖስና ከቱርክ ከፋርስ ባቢሎን መካከል የምትገኝ ስትሆን መጀመሪያ የመሠረታት ረሆቦት የተባሉ ንጉሥ ነው ቀጥሎ የኩሽ ናምሩድ የተባለው የፋርስ ባቢሎን ከተማ ቆርቋሪ ነው ከዚያም አሶር የተባለው ገናና ንጉሥ ሀገሯን ነነዌ ብሎ ከተማዋን በስሙ አሦር ብሏታል ። ከዚህ ሌላ አሸር የተባለ ሰውም ነው ተብሎ ይተረካል ።

በእሥራኤል ንጉሥ በኢላ ልጅ በሆሴዕ በይሁዳ ንጉሥ በሕዝቅያስ ዘመን በ፬ሺ.ህ ፫፻፹፯ ዓመተ ዓለም ስልምናሶር የተባለ የነነዌ ንጉሥ በሆነ ጊዜ የነነዌ ሕዝብ ከፍተኛ የሆነ ኃጢአት ሠራ ከተማይቱ ብቻ መቶ ሐያ ሺህ ሕዝብ የነበራትና በውሃ መስኖና በዝናም አማካይነት ሀብታም ስለነበረች ችግርና ጦርነት ደርሶባት የማታውቅ በመሆኗ ሕዝቦቿ በኖኅ ዘመን እንደነበሩት ሰዎች በኃጢአት ላይ ኃጢአት በመሥራት እግዚአብሔርን በጣም በደሉ ። እግዚአብሔርም በእስራኤል ከተማ ኗሪ የነበረውን የአማቴ ልጅ ዕብራዊ ዮናስ ነቢዩን የነነዌ ሕዝቦች ከልክ ያለፈ ጥጋብ ተሰምቷቸው የማይገባ ከፍተኛ የሆነ ኃጢአት በመፈጸም ላይ ስለሆኑ እስከ ሦስት ቀን የነነዌ ከተማ በእሳት ትጠፋለችና ወደ እግዚአብሔር ተመለሱ ንስሐ ግቡ ጹም ጸልዩ ፣ አልቅሱ ፣ ብለህ አስተምር ብሎ አዘዘው ።

ነቢዩ ዮናስም ጌታ ሆይ አንተ ለፈጠርከው ሕዝብ አዛኝና ይቅር ባይ ስለሆንክ እኔ አሁን ሄጄ ይህን ቃልህን ባስተምር ከሦስት ቀን በኋላ እሳት ከሰማይ ወርዶ ባያጠፋቸው ያ ሐሰተኛ ነቢይ እባላለሁና ይህን ጉዳይ ለመፈጸም አልችልም ብሎ መልስ ሰጠ ።

ጌታ ግን እኔ አንድ ጊዜ ከአፌ የወጣውን ቃሌን አልመልስምና አይሆንም ሂድ እያለ ደጋግሞ ነገረው ጧት ማታ የሚነዘንዘኝ ከፊቱ ቢያየኝ አይደለምን ብሎ ወደማያየው ሀገር ተነሥቶ ለመሔድ መጀመሪያ ኢዮጴ ደረሰ ። ለርሱ ስለመሰለው ነው እንጅ እግዚአብሔር የሌለበት ሀገር ኑሮ አይደለም ለጊዜው ዮናስ ማለት የዋህ ማለት ስለሆነ ከኢዮጴ ተነሥቶ ወደ ተርሴስ የምትሔድ መርከብ ተከራይቶ ወደ መርከ ገባ በዚያም ተስፍሮ ሲሔድ ከባሕሩ መካከል ላይ እንዳለ ማዕበል ተነሣና መርከቡን ወዲያና ወዲህ ያማታው ጀመር ።

በመርከቡ የተሣፈሩትን መንገደኞች ሁሉ ድንጋጤ ያዛቸው ማዕበሉ ጸጥ ያለ መስሎአቸው ከመርከቡ ላይ ያለውን ከባድ ዕቃ እያነሡ ወደ ባሕሩ ይወረውሩ ጀመር ። ነገር ግን ማዕበሉ ፀጥ ብሎ መርከቡ በእርጋታ ሊጓዝ አልቻለም በዚያን ጊዜ ዮናስ መርከብ ነጂ ባለበት በስተኋላ ተኝቶ ያንኮራፋ ስለነበር ሰዎች ቀስቅሰው ሀገሩንና ነገዱን የሚያመልከውን አምላክ ጠየቁት ። እርሱም በሚገባ መልሱን ከሰጠ በኋላ ችግሩ የደረሰው በእኔ ምክንያት ስለሆነ እኔን ወደ ባሕሩ ካልጣላችሁኝ በስተቀር ጸጥታና ሰላም አታገኙም አላቸው ። እነርሱም ባይሆን በዕጣ ይሁን እንጂ ሰውን ያለ ምክንያት ወደ ባሕር ወርውረን እንዴት እንጥላለን ብለው ዕጣ ቢጥሉ በዮናስ ወጣበትና ወደ ባሕር ወርውረው ጣሉት ወዲያው ከእግዚአብሔር የታዘዘ ዓሣ አንበሪ ተቀብሎ ከዋጠው በኋላ በስተኛው ቀን ወስዶ በድንገፈ ነነዌ ተፋው

ነቢዩ ዮናስም ከዓሣው ሆድ እንደወጣ ይህች ሀገር ማን ትባላለች ብሎ ቢጠይቅ ነነዌ ትባላለች አሉት በዚህ ጊዜ ጉዳዩ ገርሞት እኔ እንዲያው ደከምኩ እንጂ ለካ እግዚአብሔር የሌለበት ሀገር የለም አሁንም ፈቃዱን ከመፈጸም በስተቀር ምንም ማድረግ አልችልም አለና አሁንም ጌታዬ ሆይ የእኔን ደካማ አዕምሮዬን አየሁት ይቅር በለኝ ብሎ እግዚአብሔርን ከአመነ በኋላ እናንተ የነነዌ ሰዎች ሆይ የማይገባ ሥራ ሠርታችሁ እግዚአብሔርን አሳዝናችሁታልና የሠራችሁትን ኃጢአት ተናዘዙ ተጸጸቱ እዘኑ ጹሙ አልቅሱ ባታዝኑና ባታለቅሱ ባትጾሙ እስከ ሦስት ቀን ይህች ሀገራችሁ በእሳት ትቃጠላለች እያለ ያስተምር ጀመር ።

በዚያን ጊዜ ንጉሡ ስልምናሶር ሙሽሮች ከጫጉላቸው ይውጡ ፣ ሰው ሁሉ ወደ ሥራ አይሠማራ እንስሳት ከማደሪያቸው አይውጡ የሰውም ሆነ የእንስሳት ልጆች የእናታቸውን ጡት አይጥቡ ትንሹም ትልቁም ሰው እንስሳት ሳይቀሩ ይጹሙ ሰው ሁሉ በየአለበት ወደ እግዚአብሔር ይዘን ያልቅስ ይጸልይ የሚል አዋጅ አሳወጀ ።

ንጉሡም ራሱ ከዙፋኑ ወርዶ ማቅ ለብሶ ትቢያ ነስንሶ ከአመድ ላይ ሁኖ እስከ ሦስት ቀን እህል ውሃ ሳይቀምስ አዘነ አለቀሰ በዚህም በነቢዩ በዮናስ ስብከትና በንጉሡ አዋጅ ሕዝቡ ታዛዥ ሁኖ እስከ ሦስት ቀን ቢያዝንና ቢያለቅስ ቸር ይቅር ባይ አምላክ የነነዌን ሰዎች ጾምና ጸሎት ኀዘንና ጩኸት ምህላ ተመልክቶና ሰምቶ የታዘዘውን መዓት ወደ ምሕረት መለሰው በሦስተኛው ቀን እሳት ከሰማይ ወርዶ የታላላቅ ተራራዎችን ራስ የረዥም ዛፎችን ጫፍ አቃጥሎ ሲመለስ ታይቷል ። ይህም ምልክት የእግዚአብሔርን ቸርነት የነቢዩ ዮናስን እውነተኛነት ያስረዳል ።

በዚህም በኀብረት ሁኖ መጾም መጸለይ ማዘንና ማልቀስ በቶሎ ከእግዚአብሔር ይቅርታን እንደሚያስገኝ ለመረዳት እንችላለን ።

የነነዌ ሰዎች የሠሩት ኃጢአት ከባድ ነበር ነገር ግን ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው እግዚአብሔርን ስለለመኑ በሦስት ቀን ጾምና ጸሎት ከባዱ ኃጢአት ተደምስሶላቸው ምህረትን አግኝተዋል ። ስለዚህ ይህች የነነዌ ጾም የነነዌ ሰዎች ከተቃጣባቸው መዓት የዳኑባት ስለሆነች የእኛም ቤተ ክርስቲያን ከሰባቱ አጽዋማት አንድ ሆና በየዓመቱ እንድትጾም አድርጋለች ።

ስለዚህ የነነዌ ሰዎች ጹመው ከታዘዘ መቅሠፍት የዳኑባትን ይህችን የሦስት ቀን ጾም እንደ ጾም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ስለምታዝን ትእዛዙን ተቀብለን በየዓመቱ ጾመን ለሀገራችን ደኅንነት ለወገኖቻችን ደስታና ብልጽግናን ሰላምንና ፍቅርን በረከትን ረድኤትን ለማስገኘት እንችል ዘንድ እግዚአብሔር በቸርነቱ ይርዳን ።

---

፯ኛ/ የድንግል ማርያምን የመላእክትንና የቅዱሳንን አማላጅነት አምናለሁ አሳምናለሁ ።

፰ኛ/ ለኢትዮጵያ ሀገሬና ለኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እምነቴ እስከ መጨረሻይቱ ያለኝን ታማኝነት በቃሌም በፊርማዬም በቤተ ክርስቲያን ፊት አረጋግጣለሁ ። ለሁሉም ጸሎታችሁ ይርዳን በማለት ቃለ መሐላቸውን ፈጽመዋል ።



# የመምህር ክፍሌ ወ/ ጻድቅ አጭር የሕይወት ታሪክ

ካለፈው የቀጠለ

መምህር ክፍሌ ወልደ ጻድቅ ከማኅሌት ውስጥ ገብቶ ከመቆም ይልቅ በውጭ ሆነው ማስታወሻ በማያዝና በመጻፍ የየቤቱን ባህልና ሥርዓት እንዲሁም የጉሮሮውን ወዝ ጠንቅቆ ማወቅ ዋና ተግባራቸው ነበር ።

መምህር ክፍሌ ለመጀመሪያ ጊዜ አቋቋም ማስተማር የጀመሩት ጉንደር ግምጃ ቤት ማርያም ነው ። በዚሁ ደብር የአራቱም ጉባኤ መምህራን ባሉበት መምህር ክፍሌ ተጠርተው እንግዲህ ይህንን የያዝከውን ቃለ እግዚአብሔርና አባባል ምንም ሳታስተምር ይዘኸው እንዳትቀበር አንተን የሚመስሉ ሊቃውንትን አስተምረህ ለቤተ ክርስቲያናችን ማበርከት አለብህ ብለው ከመከሯቸው በኋላ እርሳቸውም እ'ሺ ፈቃዳችሁን እፈጽማለሁ ስለአሏቸው መርቀው ጸሎት አድርገው በንቃትና በትጋት እንዲያስተምሩ አሰናብተዋቸዋል፡ ይህም በሚፈጸምበት ጊዜ የአደባባይ ኢየሱስ መምህር የነበሩት አለቃ የማነ ብርሃን ከዚያው ስለነበሩ "እያ ክፍሌ! እንግዲህ ሀገራችን ጉንደርን በጉባኤ እናቅናት እናድሳት" ብለው ደስ ብሏቸው ተሳስመዋል ። መምህር ክፍሌ ግምጃ ቤት ማርያም በነበሩበት ጊዜም አንድ የበቁ ብሉይና ሐዲስ አዋቂ የሆኑ አባ ብዙነህ የሚባሉ የመንፈስ ቅዱስ ጓደኛ ነበሯቸው ። እርሳቸውም መገበሪያ እየለቀሙና እየሰየሙ እየፈጩ ብሉይና ሐዲስ ይተረጉሙ ነበር ። መምህር ክፍሌ ደግሞ ለእርሳቸው ውሀ በመቅዳት ሠርክ ኅብስት በማምጣት ይረዷቸው ነበር ። እኒሁ የበቁት ሊቅ የጠላት መምጣት በራዕይ ተገልጾላቸው ጠላት ጉንደርን ይወራታል ነገር ግን እኔንና አንተን እንደወንጭፍ በሚመስል መሣሪያ ወርውሮ ማኅደረ ማርያም ሲያስቀምጠን አየሁ ። እኔ ከዚህ ቦታ አልውልም አላድርም መሄዴ ነው አንተም ተከተለኝ ብለው ወደ ማኅደረ ማርያም ሄዱ ፣ መምህር ክፍሌም ከደቀመዛሙርቶቻቸው ጋር ተከትለዋቸው ሄደዋል ። በዚያም የአቋቋም ጉባኤያቸውን እያስተማሩ ከእኒሁ ከበቁት ሊቅ አባ ብዙነህ የመጻሕፍት ትርጓሜን ተምረዋል ፣ የጠላትንም ዘመን በማኅደረ ማርያም በማስተማርና በመማር አሳልፈዋል ።

ጠላት ሀገራችን ኢትዮጵያን ለቅቆ ሲሄድ የጉንደር አደባባይ ኢየሱስ መምህር የነበሩት አለቃ የማነ ብርሃን ደብዳቤ ላኩላቸው ደብዳቤውም "ለእያ ክፍሌ ወልደ ጻድቅ እንደምን አለህ? እኛ ደኅና ነን ጉንደር ቃለ እግዚአብሔር ተርባና ተጠምታ ክፍሌ ክፍሌ እያለች ታለቅሳለች ስለዚህ እስከ ፯ ቀን ድረስ ጉንደር ገብተህ ጉባኤ ዘርግተህ እንድታስተምር በጉንደር ሕዝብና በማኅበሩ ስም አማፅንሃለሁ" የሚል ነበር ይህ ደብዳቤ ለመምህር ክፍሌ እንደደረሰ የመንፈስ ቅዱስ ጓደኛቸው አባ ብዙነህ ሰምተው መልካም መልእክት ነው ሄደህ አስተምር ብለው መርቀው አቡነ ዘበሰማያት ሰጥተው የብሉይና የሐዲስ ትርጓሜን አስተምርበት ብለው መጻሕፍቶቻቸውን ሸልመው መቃብርህም ጉንደር ነው ብለው ትንቢት ተናግረው በሁለተኛው ቀን መምህር ክፍሌ ከዚያው እንዳሉ አርፈዋል ። መምህር ክፍሌም የጓደኛቸውን የቀብር ሥነ ሥርዓት በሚገባ አስፈጽመው ወደጉንደር ሄደዋል ።

መምህር ክፍሌ ወ/ጻድቅ ጉንደር በገቡበት ዕለት የጉንደር ካህናትና ሕዝብ ከፍተኛ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ለተማሪዎቻቸውም በሙሉ ሻሽ ገዝተው ሸልመዋቸዋል ። ለአንድ ሳምንትም ያህል ከእነተማሪዎቻቸው እየጠሩ ሲጋብዟቸው ሰንብተዋል ።

ከዚያ በኋላ መምህር ክፍሌ ጉባኤ አስፍተው በማስተማር በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ደቀ መኔሙርትን አስተምረው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ፣ ከእርሳቸው ተምረው የሚያስተምሩትና በመምህርነት ደረጃ የተመረቁት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ቢሆኑም በጊዜው ከምናውቃቸው የሚከተሉትን በጽሑፍ መዝግበን ለአንባብያን አቅርበናቸዋል ።


፩ኛ/ በእርሳቸው ወንበር ተተክተው በምስክርነት ጉንደር በዓታ የሚያስተምሩት መምህር ሄኖክ ወ/ሚካኤል

፪ኛ/ መሪጌታ አፈወርቅ ጉንደሮች ማርያም



www.ethiopianorthodox.org

፫ኛ/ መሪጌታ መኮንን ወገራ
፬ኛ/ ግራ ጌታ ቀለመወርቅ ጐ. በዓታ
፭ኛ/ መሪጌታ ዮሐንስ አርማጭሆ
፮ኛ/ መሪጌታ ረዳ ወገራ አሯኄ ማርያም
፯ኛ/ መሪጌታ ኢያሱ ጐንደር ከተማ
፰ኛ/ መሪጌታ ቢረሳው ጐንደር ከተማ
፱ኛ/ መሪጌታ ሠረገላ ጐንደር ከተማ
፲ኛ/ መሪጌታ መክብብ ጐንደር ከተማ
፲፩ኛ/ መሪጌታ ሠርጐ ወርቅ ጐንደር ከተማ
፲፪ኛ/ መሪጌታ ኢሳይያስ አበበ አለፋ ጠቁሳ
፲፫ኛ/ መምህር መስፍን ሸዋ እቲሳ ተክለ ሃይማኖት
፲፬ኛ/ መምህር ብርሃኑ ሸዋ ደብረ ሊባኖስ
፲፭ኛ/ ርእሰ ደብር ግርማ አበበ ሸዋ ወንጂ እማ ሸንኮራ ኪዳነ ምህረት
፲፮ኛ/ ሊቀ ካህናት ቀለመወርቅ ሸዋ ናዝሬት ቅ/ማርያም
፲፯ኛ/ መሪጌታ ኤፍሬም ሸዋ ኡፈሶን
፲፰ኛ/ መሪጌታ ብርሃኑ ጌጡ ሸዋ መንዝ
፲፱ኛ/ መጋቤ ስብሐት መልአኩ ፈለቀ አዲስ አበባ
፳ኛ/ መምህር ሀረገወይን አዲስ አበባ
፳፩ኛ/ መምህር መርሐ ጽድቅ ኮከብ አዲስ አበባ
፳፪ኛ/ ሊቀ ጠበብት መዝገቡ ሀብተ ገብርኤል አዲስ አበባ መንበረ መንግሥት ቅ/ገብርኤል
፳፫ኛ/ መሪጌታ ዕዝራ ገነት አዲስ አበባ መንበረ መንግሥት ቅ/ገብርኤል
፳፬ኛ/ መሪጌታ ወልደ ዳዊት ቸኮል አዲስ አበባ
፳፭ኛ/ መሪጌታ ሞገስ ኪዳነ ማርያም አዲስ አበባ
፳፮ኛ/ መሪጌታ ሐዲስ ሐዋርያ አዲስ አበባ ጐላ ሚካኤል
፳፯ኛ/ መሪጌታ አክሊሉ አዲስ አበባ
፳፰ኛ/ መልአከ ሰላም ወርቁ ውብ እሸት አዲስ አበባ
፳፱ኛ/ ሊቀ ጠበብት ትርሲት ቂርቆስ መካነ ሰማዕት
፴ኛ/ መሪጌታ አምሳሉ ጐጃም
፴፩ኛ/ መሪጌታ አዲስ አበበ ትግራይ
፴፪ኛ/ መሪጌታ ዓይነ ኩሉ ትግራይ
፴፫ኛ/ መሪጌታ ጥዑመ ልሣን ትግራይ
፴፬ኛ/ መሪጌታ ዕንቁ ባህርይ ደሴ



መ ክፍሌ ወልደ ጻድቅ ዜቁን ያዘጋጁበት የአባ ጃሌ ተክለሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን

፴፭ኛ/ መሪጌታ አሰፋ ገብረ መድኅን የጁ
፴፮ኛ/ መሪጌታ አስካል ሰቆጣ
፴፯ኛ/ መሪጌታ ሰሎሞን ላስታ
፴፰ኛ/ መሪጌታ ልሣነ ዕፍረት ላስታ
፴፱ኛ/ አፈ መምህር ሀረገወይን ረታ ላስታ
፵ኛ/ መሪጌታ ሙሴ ኤርትራ ወዘተ ናቸው ።

ከመምህር ክፍሌ ወልደ ጻድቅ የተማሩትን መምህራን በዝርዝር አቀርባለሁ ማለት የሰማይን ከዋክብት እቆጥራለሁ ብሎ እንደመቃጣት ስለሚቆጠር ጽሑፋችን በአጭሩ ገተነዋል ።

መምህር ክፍሌ በቅኔ በኩልም እጅግ በጣም የተራቀቁና አገባብም አዋቂ በምሥጢር ተራቃቂ በመሆናቸው የሚቀኟቸው ቅኔዎች ሁሉ አስደናቂዎች ነበሩ ከተቀኟቸውም ቅኔዎች ቀጥለን አቅርበናል ።

የሆሣዕና ዕለት የተቀኙት መወድስ ቅኔ
ስኩራኑ ቅንዓት አይሁድ ውሉደ አመፃ
ለመዝሙረ ዳዊት
አልዓዛር ዓይኔ ቀበርከምዎ
ሆሣዕና ዳዊት ንባበ ዘታረምምዎ
አምጣነ ያነሥእ ቅድሜክሙ ነቢየ ዕብነ ቢታንያ ወሎቱ ስምዕዎ ወበፍና ኪሩብ ተቀበልዎ ለርእሰ ማዕዘንት ዕብነ ንጸቅት ዘመነንዎ
ለመስብክትሂ ዕብነ ሳሌም እስከነ አፋሁ ምልዕዎ
መዝሙረ ስብሐት ማየ ቅዳሴ ሱራፌል እንተ ቀድሕዎ
ውሂዘ መሐላ መስቀለ እንተ ወልደ አብ አደዎ ቅሩብ ትኢጽሩ ወርሁቀ ትርአይዎ

ለታኅሣሥ በዓታ ዋዜማ የተቀኙት ዋዜማ ቅኔ
ለፈትል ውሂዘ ማይ ፣ ራቆ ኢይስተይ እጽባዕተ ድንግል ምእመን
ተቶስሐ ወርቀ ተዋህዶ ዘገለአድ ወይን ወእንዘ ቅድሐቱ ምሉዕ ጽዋዓ ንጸሬ ዘዓይን



ለዝኒ ጽዋዕ መንክር ጥዑመ ልሣን አንከርዎ ከናፍር ኄራን

መምህር ክፍሌ በሕይወታቸው ሳሉ ሊሞቱ አቅራቢያ ዘመዶቻቸው መጥተህ እየን የሚል ደብዳቤ ልከውላቸው ነበርና ለዚያ መልስ ሲጽፉ ከደብዳቤው ጋር ጽፈው የላኩት ጉባኤ ቃና "ዕቅፍትየ ኮነት ተፈልጦትየ እምጥንት ፍቅረ አሐቲ ጐንደር እስመ ከመ ሞት ጽንዕት" ትርጓሜው

ከጥንት ጀምሮ መለየቴ እንቅፋት ሆነችብኝ የጐንደር ፍቅር ከሞት የጸናች ናትና ማለት ነው ።

መምህር ክፍሌ ወልደ ጻድቅ የቀለም ትምህርት ብቻ ሳይሆን ተግባረ እድም አዋቂ ስለነበሩ መጻሕፍትን እየጻፉ በሚያገኙት ገቢ ከደቀ መዛሙርቶቻቸው መካከል ራሳቸውን ለመርዳት የማይችሉትን በልብስና በምግብ ይረዱ ነበር ሚስት አግብተው ትዳር መሥርተው ለመማር ለሚመጡትም ሌት ከቀን አስተምረው ቤተ ክርስቲያኑን የሚያገለግሉበት ዚቅና መዝሙር ጽፈው በቀላል ዋጋ እየሸጡ በቶሎ ወደ ቤታቸው እንዲመለሱ ያደርጉ ነበር ።

መምህር ክፍሌ ከማስተማር ተግባራቸው ጋር የተጣላ ማስታረቅ የታመመ መጠየቅ የታሠረውን ዋስ ሆኖ ማስፈታት ያዘነውን ማጽናናት ላጣው መርዳት የተለመደ ተግባራቸው ነበር ከእርሳቸው ገንዘብ የተበደረ ሰው አስቦ ካልሰጣቸው ስጠኝ ማለትን አያውቁም ነበር ።

መምህር ክፍሌ ከሚኖሩበት ቤታቸው ውስጥ በርከት ያሉ የውሀ መቅጃዎችን ኮዳዎች አዘጋጅተው በማስቀመጥ ሌሊት ሰው ሳያያቸው ውሃ ቀድተው በማምጣት ማታ ማታ ውሀ የጠማው ተማሪ እንዲጠጣ ያደርጉ ነበር ።

መምህር ክፍሌ ወልደ ጻድቅ መምህረ ትሕትና ወፍቅር እንደመሆናቸው መጠን በአለባበስም ሆነ በአቀማመጥ ከተማሪዎቻቸው የተለየ ክብር አይፈልጉም ነበር ።

እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብኩ እናንተ ደግሞ እርስ በእርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ለሌላው ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁ ያለውን ቃል በተግባር ለመግለጽ ተማሪዎቻቸው ሩቅ ሀገር ሄደው ሲመለሱ እንግዳ ሲመጣ እግር ማጠብ ምግብ አዘጋጅቶ ማቅረብ የተለመደ ተግባራቸው ነበር ። ዮሐ. ፲፫.፲፬ ።

መምህር ክፍሌ በሚያስተምሩበት ጊዜ ደከመኝን ሰለቸኝን የማያውቁ የማስተማር መንፈሳዊ ኃይልም ስጦታ የነበራቸው ከአፋቸው ክፉ ቃል የማይወጣ ርኅሩኅና ደግ መምህር ነበሩ ስለ ዚህ ነው ተቆጥረው የማያልቁ ደቀ መዛሙርትን አስተምረው አሰልጥነው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አስረከበው ያለፉት ።

መምህር ክፍሌ ወ/ጻድቅ ትሁት ርኅሩህ ንጹሕ ድንግል በጠቅላላው ይህ ቀረህ የማይባሉ የጥበብ ምንጭ የሆኑ መንፈሳዊ አባት ነበሩ ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ፲፪.፴፫ ዛፍ በፍሬው ይታወቃል ብሎ እንደተናገረው የእኒህም መንፈሳዊ አባት የሥራ ፍሬ አስተምረው ባወጧቸው ምሁራን ታውቋል ።

መምህር ክፍሌ ጐንደር ከተማ ወንበራቸውን ዘርግተው ጉባያቸውን አስፍተው ከምሥራቅ ከምዕራብ ከሰሜን ከደቡብ ለመማር የሚመጡትን ደቀ መዛሙርት ባዕድ ዘመድ ወዳጅ ጠላት ሳይሉ ሁሉንም እንደልጅና እንደወንድም በመመልከት ያስተምሩ ነበር ።

በሚያስተምሩበትም ጊዜ ከመ ኢይበውዕ ውስተ ጽላሎተ ቤትየ ወከመ ኢየአርግ ውስተ አራተ ምስካብየ ወከመ ኢይሁቦን ንዋመ ለአዕይንትየ "ብሎ ክቡር ዳዊት እንደተናገረው ከቤተ ገብቼ ልረፍ ከአልጋዬ ወጥቼ ለዓይኖቼ እንቅልፍ ላድርግ አይሉም ነበር ሊቀ ጽድቅን ከኃጢአት ሃይማኖትን ከክህደት ለይተው የሚያስተምሩ ንጽሕናቸው ቅድስናቸው ትሕትናቸው መምህርነታቸው እንደፀሐይ የሞቀ እንደጨረቃ የደመቀ ነበር ሐዋርያው ጳውሎስ "መልካም ገድልን ተጋድያለሁ ሩጫዬንም ጨርሻለሁ ሃይማኖቴንም ጠብቂያለሁ ወደፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ይህንም ኮናኒ በርትዕ ፈታሒ በጽድቅ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ ያስረክበኛል ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም ። ብሎ በ፪ኛ ጢሞቴዎስ ፬.፯ እንደ ተናገረው በተወለዱ በ፶፱ ማስተማር በጀመሩ በሰላሣ ሰባት ዓመታቸው ኅዳር ሰባት ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ.ም. አርፈው ለብዙ ዓመታት ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው ሲያስተምሩበት በኖሩበት በዓታ ደብረ ኃይል ተቀብረዋል ።

በቀብሩም ላይ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ካህናት ሊቀ አእላፍ በላይ መርሻ የ፵፬ ጐንደርአድባራትናገዳማትሊቃውንት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምእመናን ተገኝተው ነበር ። ሞት ሥጋ ለለበሰ ሁሉ የማይቀር የሥጋ ዕዳ ነው ነገር ግን መልካም ሥራ የሠራ ሰው የማይሞት ታሪክ ተክቶ ስለሚያልፍ ለሁልጊዜ ሲታወስ ይኖራል እንደመምህር ክፍሌ ያሉትን ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያናችን ምንጊዜም አትዘነጋቸውም ከቅን አገልግሎታቸውና ከመልካም ሥራቸው ጋር ታሪካቸውን መዝግባ ስታስታውሳቸው ትኖራለች ።

የዜናው አቅራቢ ቄ. ልሣነ ወርቅ
በዛብህ



www.ethiopianorthodox.org

# የቤተሰብ ዓምድ

## የልጅ አስተማሪ

ታሪክ እንደመስተዋት

ወረዳው አቃቂ ቀበሌው ደወራ
የታሪክ ተጠሪ አቶ ዳዲ ብራ ፡
በልጅነታቸው የሠሩት ቁም ነገር
ታሪኩ ባጭሩ እንዲህ የሚል ነበር ፡
አቶ ብራ አብሴ የአቶ ዳዲ አባት
ቤት ንብረት መሥርተው ሲኖሩ
በሥርዓት ፡
ወላጅ አባታቸው አቶ አብሴ አርጅተው
ያላቸውን ንብረት ስላወረሱአቸው ።
ባለጸጋ ሆነው ወለድ በማበደር
ከአባታቸው በልጠው ከፍ ብለው
በመንደር
በዘፈን በሆታ ይሞገሱ ነበር ።
አባታቸውንም ሰብስበው ሲጦሩ
ነግ በእኔ ሳይሉ ምንም ጡር ሳይፈሩ
ከሣር በተሠራች ጐጆ ውስጥ አኑረው
የማድቤት ከሰል የምግብ ማብሰያው
ዕንጨቱ ኩበቱ እየጨሰባቸው
በሽምግልና ዕድሜ ጥርስ ሳይኖራቸው
የባቄላ አሹቅ ሽምብራ ቆርጥመው
ከዚህም ጋር ጥጆች እየረገጡአቸው
ይኖሩ ነበረ ደባደቦ ለብሰው ።
ጌታው አቶ ብራያ ከደጉ አባታቸው
ባገኙት ብዙ ሀብት ሲኖሩ ተዝናንተው
መካንነት ብቻ ብዙ አስጨነቃቸው ።
ጐልማሳነት አልፎ ዕድሜያቸው ሲገፋ
ወንድ ልጅ ወለዱ ለመለመች ተስፋ
ስሙን ዳዲ ብለው እያንቀባረሩ
ያንን የሥዕለት ልጅ ደክመው በሸሩሩ
እያሞላቀቁ ተከባክበው ይዘው
ማሳደግ ጀመሩ እጅግ ደስ አላቸው ።
ዕድገቱም ቀጥሎ ገና አፉን ሲፈታ
ከርሱው ጋር ሆነ ሣቅና ጭዋታ
ታዲያ አቶ ብራ ከዕለታት አንድ ቀን
እንደመኩራት ብለው እንደመዘባነን
"ዳዲ እስቲ ተመልከት የማደርግል
ህን
ለራሴ ሳልማር እያስተማርኩ አንተን
እንዲህ አሳምሬ ያሠለጠንኩህን
ታዲያ አንተስ በተራህ እኔን አባትህን
ሳረጅ የምትጦረኝ እንዴት አርገህ ይሆን?
ብለው በማጠንከር ጠየቁት በፈሊጥ
ዳዲም በበኩሉ አጭር መልስ ሲሰጥ
"አንተን የምረዳህ የምጦርህ በዕርግጥ
ልክ አንተ ለአባትህ እንደምታደርገው
ሳልቀንስ ሳልጨምር በማመጣጠን ነው
ለአያቴ ለአበባ አንተ እንዳደረግህ
በትንሽ ማድቤት ውስጥ ሰሌን አንጥፈ
ልህ
ዕላቂ ቡትቶ ደባደቦ ለብሰህ
ቁንጫና ትኋን እየዘለለብህ
ላቁመተ ሥጋ ቆሬሽ እያገኘህ
ሽምብራ ቆርጥመህ መኖር ትችላለህ
ይኸውነው ለአባትህ ስታደርግየማይህ
አንተስ ከዚህ ሌላ ምን ትጠብቃለህ
እያለ በሲቃ ተናግሮ ሳይጨርስ
ከዳዲ ባገኘው የማያዳግም መልስ
አቶ ብራ አብሴ ገርሞአቸው ነገሩ
በፈጸሙት በደል መጸጸት ጀመሩ ።
በርግጥም ከዚያ ልጅ ቁም ነገር ተማሩ
ወደ አባታቸውን ከማድ ቤት አወጡ ፡
ድንክ አልጋ ዘርግተው በዕልፍኝ አስቀ
መጡ ፡
ሰሌን ተለውጦ ደባደቦው ቀርቶ
በእሳት ተቃጠለ ያ ሁሉ ቡትቶ

የምሳሌው ትርጉም


ታሪክ መስተዋት ነው የማያሳስት
እኛነታችንን የምናይበት
ከሆነ አይቀር ይህ ነው የልጅ አስተማሪ
ምንም ቃል ሳይደብቅ ያየውን መስካሪ
ከዚህም የሚብስ ብዙ አለ አሳፋሪ
ብዙ ልጆች ወልደው ማሳደጊያ ሲያጡ
ቃሪሚያ እየማረሩ ቅጠል እየሸጡ
ከአፋቸው ነጥለው ሳይበሉ እያበሉ
ልጆች በማሳደግ ውለታ የዋሉ
ለማዕርግ አብቅተው የዳሩ የኳሉ
የሀገር አለኝታዎች ስንት ወላጆች አሉ ።
ታዲያ በዕርጅናቸው ደክመው ሲቸገሩ
ያን ሁሉ ቁም ነገር ውለታ እንዳልሠሩ
ጧሪ ቀባሪ አጥተው እንዴት መና
ይቅሩ ?
መርዳት የሚችሉ ልጆች እያላቸው
ቀድሞ ያላዩትን የሰው እጅ አይተው
በችግር ለመኖር እየተገደዱ
የወላድ መካኖች ሆነው የተጐዱ
አልፎ አልፎ አይታጡም ግልጥ ነው
ልማዱ ።
አንዳንድ ወላጆችም ነግ በእኔን ረስተው
የወጭ ድንክ አልጋ የቤት ቀጋ ሆነው
ወላጆቻቸውን በማጉላላታቸው
እነርሱም በፋንታ ዕርጅና ሲያንቃቸው
በሠፈሩት ቁና ቢሠፈርባቸው
እንዳይፀፀቱ ኋላ እንዳይቆጫቸው
ይህ አጭር ምሳሌ ትምህርት ይሁና
ቸው ።

መ/ አዕ መክብብ አጥናው



# ከዋሻ ውስጥ የተሠራችው የደብረ ዘመዶ ማርያም ገዳም ታሪክ

ደብረ ዘመዶ ማርያም ገዳም በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ ውስጥ በራያ ቆቦና በዋግ አውራጃ አዋሳኝ የምትገኝ አስደናቂ ገዳም ናት ዘመዶ ማለት የማርያም ዘመድ ገዳም ማለትም ልዩ ልዩ ዕፀዋት የበቀሉበት ጫካ ማለት ነው በሌላ በኩል ደግሞ መናንያን መነኮሳትና ባሕታውያን የሚኖሩባት ማለት ነው ከላይ ስሟ የተጠቀሰችው ገዳም በልዩ ልዩ ዕፅዋት በወይራ በጥድ በሾላ በዋርካ በታሎ በመሳሰሉት ዕፅዋት የተከበበች የለሚ የትርንጐ የወይን የጌሾ የመሳሰሉት አትክልት ያላት ናት ፡ ከዱር አራዊቶችም ነበር ፡ ድኩላ ፡ ስስ ሚዳቋ ፡ ቆቅና ጅግራ ንብ ጣዝማ የሚረቡባት ከተራራ ጥግ ሁና ከዋሻ ውስጥ ተገንብታ የተሠራች አስደናቂ ቤተ መቅደስ ናት ገዳሟ የተቆረቆረችው በዘጠኝ መቶ ሰማንያ ዓ.ም. ነው በመካከል ላይ ግን ገዳምነቷ ከመጥፋቱ የተነሣ አንድ ዮናስ የሚባል ሰው ከሚስቱና ከዘመዶቹ ጋር ሁኖ የቀንድ ከብት እያረባ መኖሪያ ቤት አድርጓት ኖሯል እርሱ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየም በኋላ ሚስቱ ከቤተ ሰቦቿ ጋር በመሆን ከብቶቿን ስታረባበት ብዙ ዘመን መኖሯ ይነገራል ከብዙ ጊዜ በኋላ ግን ጻድቁ አቡነ በርተሎሜዎስ በፈቃደ እግዚአብሔር ወደዚች ቦታ መጥተው የመነኮሳትና የባሕታውያን መኖሪያ ለማድረግ ዕቅድ ካወጡ በኋላ ያችን ዘመድ የተባለችውን ሴትዮ እኅቴ ሆይ ይህች ቦታ ለመነኮሳትና ለባሕታውያን መኖርያ እንድትሆን ከእግዚአብሔር ዘንድ የተመረጠች ስለሆነች ሌላ ቦታ ይዘጋጅልሽና በዚያ ከብቶችሽን እያረባሽ ተቀመጭ ብለው አሳብ አቀረቡላት ሴትዮዋ ግን እኔ ምንም ቢሆን ይህችን ቦታ አለቅም ብላ እንቢ አለች ጻድቁም ወደ እግዚአብሔር ቢአመለክቱ መላእክት ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዘው ሌሊት ከከብቶቿ ጋር እንደተኛች ሲአል ሜዳ ተብሎ ከተጠራው ቦታ ዋካት ላይ ከነጓዟ አንሥተው አሠፈሯት በማግሥቱ ሲነጋ ከእንቅልፏ ባና ብትነሣ ነፋስና ብርድ የበዛበት የማታውቀው ቦታ ሆኖ ስለአገኘች ምን ሲኦል ቦታ ነው ስትል በመስማቷ ሲኦል ሜዳ



የደብረ ዘመዶ ቤተ ክርስቲያን በዋሻ ውስጥ

ተብሎ ቦታው ይጠራ ጀመር ሴትዮዋም የእግዚአብሔር ትእዛዝ መሆኑን አውቃ ጻድቁ አቡነ በርተሎሜዎስን ይቅርታ ጠይቃ እንዲህ ብላ ለመነች አባቴ ሆይ ቦታዋ በእኔ ስም ትጠራልኝ እባክዎ ብላ ስለለመነች ጻድቁም ይሁንልሽ ባንቺ ስም ትጠራልሽ ብለው ተስፋ ስለሰጧት ደስ ብላት ተመለሰች ቦታዋም ደብረ ዘመዶ ተባለች ይባላል ። ከዚህ ዕለትም ጀምረው ጻድቁ አቡነ በርተሎሜዎስ መነኮሳትንና ባሕታውያንን እየሰበሰቡ የአንድነት ገዳም ማቋቋም ጀመሩ መነኮሳቱ እየበዙ ሲሔዱ ድጋፍ ከመንግሥት የሚያስፈልጋቸው ስለሆነ ሄደው በዘመኑ ነግሠው ለነበሩት ለዓፄ ይኩኖ አምላክ ያቋቋሙትን ገዳም እንዲገድሙላቸው ጠይቁአቸው ዓፄ ይኩኖ አምላክም የጻድቁን ቃል በማክበር በሠራዊቱ ታጅበው ሔደው ቦታውን ከተመለከቱ በኋላ በዋሻው ውስጥ ታላቅ ቤተ መቅደስ እንዲሠራ አዘው አስደናቂ ቤተ ክርስቲያን ተሠርቷል የአሠራሩም ሁኔታ በግንብ ሁኖ በግንዱላ እንጨት አልፎ አልፎ እንደመቀነት በማስታጠቅ ውስጡን የእንጨት ጣውላ ኮርኒስ በማድረግ በልዩ ልዩ ሐረግና ምሳሌ በማስፈልፈል በባንዲራ ቀለም አስጊጠው መስኮቶቹን በጌሾ በተጣበቁ ዕብነ በረድ መሰል ድንጋዮች በልዩ ልዩ ጌጠኛ ሐረግ በማስፈልፈል ካሠሩ በኋላ ብዙ ርስት ጉልት ከንዋየ ቅድሳት ጋርና የራሳቸውን የወርቅ ወንበር በመሸለም ዳሯ እሳት መሐሉ ገነት ትሁን የሠገረ ቆቅ የበረረ ዎፍ መናኛ እንዳይታደንባት ትሁን ብለው የእመቤታችንን ማርያምን ታቦት አስገብተው ቅዳሴ ቤቷን በማክበር በጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖትና በአቡነ በርተሎሜዎስ አስወግዘው በአንድ ሺህ ፪፻፸ ዓ.ም. ገዳም አደረጓት ከዚህ ዘመን ጀምሮ ገዳሟ እየገነነች ሄደች ።



www.ethiopianorthodox.org

ጻድቁ አቡነ በርተሎሜዎስም በዚች ገዳም ብዙ ትሩፋት ሠርተውባታል ጠቅላላ የገዳን ወረዳ የቆባ ጠጠራና የኮረም ወረዳ ሊቀ ካህናትና ኢጲስ ቆጶስ ሁነው በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ፈቃድ ተሾሙ በነዚህ ወረዳ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት በማጠናከር ብዙ መንፈሳዊ ሥራ አበርክተዋል በገዳሟ ውስጥ ብዙ መንፈሳዊ ነገሮች በብቃታቸው በትሩፋታቸው አበርክተዋል በጸሎታቸው ብዙ ምንጮች ፈልቀዋል ብዙ ተአምር ሠርተዋል በስማቸው ጸበል ፈልቆላቸዋል በዚህ ቅድስና ሥራቸው ክርስቶስ ከፍተኛ የምህረት ቃል ኪዳን ሰጥቷቸዋል በመጨረሻም በተወለዱ በመቶ ሰባ ዘመናቸው ጥቅምት አራት ቀን አርፈው በዚችው በደከሙባት በደብረ ዘመዶ ማርያም አርፈው ቅዱስ ሥጋቸው በቤተ መቅደሷ ውስጥ ከክብር ቦታ ተቀብሮአል ።

የቅድስና ሥራቸውንም የሚገልጽ ገድል ተጽፎላቸዋል ከዚህ ዘመንም ጀምሮ ገዳሟ በየጊዜው የነገሡ ነገሥታትና የተሾሙ ጳጳሳት እየተንከባከቧት እንደከበረች ትገኛለች በገዳሟም እየተረዱ የቅዳሴ የዜማ የቅኔ ያቋቋም መምህራን ተቀምጠው ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍርተውበታል የሥዕልና የቁም ጽሕፈት ሚያ ያላቸውም በገዳሟ ተቀምጠው ብዙ የብራና መጻሕፍቶችና ሥዕሎች ሐረጎች እየሠሩ ለገዳሟ ስለአበረከቱት ዛሬ ይህች ገዳም በበራና የተጻፈ የብሉያትና የሐዲሳት የሊቃውንትና የገድለ ሰማዕታትና ጻድቃን ጠቅላላ የታሪክ መጻሕፍት የሚገኙባት ታላቅ ገዳም ናት ነገሥታትና ጳጳሳትም የሰጧት የወርቅና የብር የመዳብና የብረት የእንጨት ፃሕል ጽዋዕ መስቀል ጽንሐ ቃጭል መረዋ ከበሮ ጽናጽል ቁጥሩ ከ፳፻ በላይ ይሆናል ።

ከአቡነ በርተሎሜዎስ በኋላም አባ ዮሐንስ የሚባሉ ጻድቅ ተተክለው ለገዳሟ ብዙ መንፈሳዊ ትሩፋትን ሠርተውላታል ።

ኒእ ዘም ጻድቅ ወደ ገዳሟ የመጡት በዓፄ ናዖድ ዘመነ መንግሥት ነው እሳቸውም ብዙ የቅድስና ሥራ በቦታዋ ሰርተዋል የምህረት ቃል ኪዳን ተቀብለው ሐምሌ ፴ ቀን አርፈው በዚሁ ገዳሟ ውስጥ በክብር ተቀብረዋል የመቃብራቸውም አፈር ለልዩ ልዩ ደዌ መድኃኒት በመሆን የታመመ እየተቀባ ይፈወስበታል በልዩ ልዩ ሐረግ ተፈልፍሎ የተሠራ ወንበራቸውም ይገኛል ዓፄ ናዖድ ቤተ መቅደሷን አድሰው ብዙ ንዋየ ቅድሳት ሰጥተዋታል ዓፄ ናዖድ ያደሷትን ገዳም በ፲፰ኛው መቶ ዘመን በዓመፅ ተነሥቶ የነበረው ግራኝ መሐመድ የገዳሟን ንብረት ለመዝረፍና ገዳሟን ለማጥፋት ወደ ደብረ ዘመዶ ማርያም ሒዶ ከገዳሟ ሲደርስ በተአምር በየጥዱ የሚገኘው ንብ ተነሥቶ ስለአስደነገጠው አንድም ጥፋት ሳያደርግ ተመልሶአል አሁን በቅርብ ጊዜም በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. ላይ ኢጣልያ ፋሽሽት ኢትዮጵያን በመውረር መጥቶ ሣለ የገዳሟን ንብረት ለመዝረፍና ገዳሟን ለማጥፋት ዘምቶ ነበር እንደዚሁ በግራኝ እንደተደረገው ተአምር የንብ ሠራዊት እየነደፈ ስለአባረረው ገዳሟ አሁን ከፍተኛ የሆኑ ጥንታውያን ቅርሳ ቅርሶች አሏት መናንያን መነኮሳትም እንደ ጥንቱ የአንድነት የንፍሮ ገዳምነቷን በማጠናከር ላይ ናቸው በአሁኑም ጊዜ ከ፲፱፻፸፩ ዓ.ም. ጀምሮ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ መልካም ፈቃድ ገዳሟ እየተረዳች የጥንት ባሕሏን ሳትለቅ በሰላም ትገኛለች ገዳሟ የብርድ ኃይል የሌላት ከጥግ ቦታ የተመሰረተች ጭት ውሃ ጩበረት ውሃ ማይ መቅጃ ሽስግግ ውሃ መሰለሚያ ውሃ የሚባሉ ምንጮች በብዛት ያሏት ዓፀዶቿ ያልተደፈሩ በዓፀዶቿ ብዛት ግርማ ሞገስ ያላት በራስ ዓንባ ኢየሱስና በቀራጥ ማርያም በቆባ ጠጠራና በዋካት ሚካኤልና በመሐጉ ማርያም በሚባሉ ታላቅ ቦታዎች የታጠረችና የተከበበች ናት ደብረ ዘመዶ ገዳም ዓመት እስከ ዓመት ሰዓታትና ቅዳሴ ጸሎተ ዕጣን የማይታጐልባት ብዙ መንፈሳዊ ትሩፋት የሚሠራበት ታላቅ ገዳም ናት ደብረ ዘመዶ ማርያም ለመናንያን መኖሪያ አመች የሆነች የኑሮ ችግር የሌለባት ጸጥታና ሰላ



ጻድቁ አቡነ በርተሎሜዎስ

ም የሰፈነባት አየሯ ተስማሚ ቅድስት ቦታ ናት ወደዚህች ገዳም ሔዶ መጐብኘት ትልቅ ጸጋ ነው ምክንያቱም ከቦታዋ ማማር ሌላ ጥንታውያን የታሪክ መጻሕፍቶችን አንብቦ ለመረዳት ይቻላል በምናኔም ለመኖር የፈለገ የአንድነትና የንፍሮ ገዳም ስለሆነ አመች ቦታ ናት ከዚህ ሌላ ሉቃስ የሣላት የእመቤታችን ሥዕል ከኢየሩሳሌም በአባ ዮሐንስ እጅ መጥታ በገዳሟ ትገኛለችና ይህችንም ሥዕል በዓይን ማየት ትልቅ ጸጋ ነው ሥዕሏ የ12ቱን ሐዋርያትን ሥዕል ደርባ ይዛ ትገኛለችና ይህችንም ሥዕል መማፀን መልካም ዕድል ነው እንላለን የደብረ ዘመዶ ገዳም መሥራች የሆኑት አቡነ በርተሎሜዎስ በጥቅምት 4 ቀን የዕረፍታቸው ቀን ስለሆነ ይከበራል ሉቃስ የሣላት የእመቤታችን ሥዕል ግንቦት አንድ ቀን የገባችበት ስለሆነ ይከበራል ሐምሌ 30 ቀን ገዳሙን በተከታታይ ያደሱአት የጻድቁ ዮሐንስ ዕረፍት ስለሆነ ይከበራል በነዚህ ቅዱሳን መቃብር ቦታ ላይም መጸለይ መልካም ነው ስለዚህ ይህችን ቅድስት የሆነች ገዳም እንጐብኝ ።

አቅራቢ. አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ
ዘገነተ ማርያም



# በሰላም አሰናብተኝ

ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወት በሰላም እንድሄድ አሰናብተኝ ብሎ የተናገረው የብሉይ ኪዳን ካህን ስምዖን ነበር ። አሸናፊ ኃያል ተብሎ የተጠራ በጥሎሞስ የሚባል ንጉሥ በጦርነት እያሸነፈ ግዛቱን በአስፋፋበት ዘመን ሕዝበ አይሁድ ለሥልጣኑ ተንበርክከው ነበር ። ከአይሁድ ሊቃውንትና መምህራን መካከል ሰብዓ ሊቃውንት ተመርጠው መጻሕፍተ ብሉያትን ከዕብራይስጥ ወደ ድርዕ ቋንቋ እንዲተረጉሙ በዘመኑ አዟቸዋል ። ይህም የሆነው የአይሁድ አረታዊ ሕግ ለሁሉም እንዲዳረስ የእግዚአብሔር ፈቃድ በመሆኑ እንደነበር ግልጽ ነው ። ሊቃውንቱ በኅብረት መተርጐማቸው ቀርቶ በየራሳቸው እንዲተረጉሙና የተረጐሙት እየቀረበ በሊቃውንት ጉባኤ እንዲመረመር ልዩ ትዕዛዝን ሰጥቷል ።

ሊቃውንቱንም በሰላሳ ሰባት ድንኳኖች ከፋፍሎ በመመደብ ሥራቸውን እንዲቀጥሉ አድርጓል ፤ የሚጠብቋቸውንም ወታደሮች ሰይሟል ፤ ከሰብዓ ሊቃናት መካከል አንዱ ትልቅ ዕውቀት የነበረው ታላቁ ሊቅ የካቲት ስምንት ቀን ዕለተ ልደቱ የሚታሰብለት ካህን ስምዖን ነበር ። በበጥሊሞስ ንጉሣዊ ትእዛዝ መሠረት ካህን ስምዖን መጻሕፍተ ብሉያትን ሲተረጉም ከመጽሐፈ ኢሳይያስ ትርጓሜ ሲደርስ "ናሁ ድንግል ትጸንስ ፣ ወትወልድ ወልደ ወትሰምዮ ስሞ አማኑኤል" (ትንቢተ ኢሳይያስ ፯.፲) ድንግል ትጸንሳለች ወንድ ልጅንም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች የሚለው ቃል በጣም አውኮታል ። ትክክለኛ የነቢዩን የትንቢት ቃል ተርጉሞ ቢያቀርብ በጥሊሞስ እንደሚዘብትበትና ቃሉን በሐሰት ለውጦ እንደተረጐመው አድርጐ በማሰብ ይቀጣኛል ብሎ አሰበ ፣ ፈራ ። ድንግል ያለዘርዓ ብእሲ እንዴት መውለድ ትችላለች ? በማለት ርሱ ራሱም ተጠራጠረ ። በዚህ ታላቅ የሃሳብ ማዕበል ተመትቶ ሲጨነቅና አእምሮው ሲዋልል "ድንግል" በማለት ፈንታ "ወለት" በማለት ጽፏል ። በዚህ ጊዜ በድንገት ከባድ እንቅልፍ ጣለውና ተኛ ሲነሳ እርሱ የጻፈው ተደምስሶ "ድንግል" የሚል ቃል ተጽፎ አገኘቶታል፣ ይህ የተፈጸመው ሦስት ጊዜ ነው በመጨረሻውም መልአከ እግዚአብሔር እንዲህ አለው ። "ተጠራጥረሃልና ከቅድስት ድንግል ማርያም እንበለ ዘርዓ ብእሲ የሚወለደውን ክርስቶስን ሳታይ ሞትን አትቀምስም ፣ በክንዶችህም ትታቀፈዋለህ" በማለት ነግሮታል ። ከእንቅልፉ በነቃ ጊዜም በራዕይ ስለሰማው የምስራች እጅግ በጣም ተደንቆ ፈጣሪውን አመስግኗል ። ከዚያች ዕለት ጀምሮ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስከተወለደበት ጊዜ ድረስ ሁለት መቶ ዓመታት መቆየት እንደቻለ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ ። በአጠቃላይ ዕድሜው አምስት መቶ ዓመታት እንደነበር ተጽፏል ። ከእርጅናው ጽናት የተነሳና የእግዚአብሔርም ክብር እንዲገለጽ አረጋዊ ስምዖን ዓይኖቹ ታውረው ነበር ። እግዚአብሔር መልአኩን ልኮ የገለጠለት ይፈጸም ዘንድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ተወለደ በተወለደ በአርባኛው ቀን እናቱ ቅድስት ድንግል ማርያምና ዮሴፍ ሌሎችም አዝማደ ማርያም ሕፃኑን ኢየሱስን በኦሪት ሕግ መሠረት ዕጉለ ርግብ ፣ ዘውገ ማዕነቅ ይዘው ወደ ቤተ መቅደስ ሄዱ ። ወደቤተ መቅደስ እንደገባም ስምዖን ተቀብሎ አቀፈው ። በአቀፈው ጊዜ የታወሩ ዓይኖቹ በሩ ፣ የደነገዘ ጉልበቱ ተፍታታ ፣ ታደሰ ከዚህ ጊዜና ሰዓት ያደረስኸኝ ከደዌዬ የፈወስኸኝ ብሎ እግዚአብሔርን አመሰገነው ።

"ባሪያህን በሰላም ልታሰናብተው ይገባል" ፃር ጋር ሳይጸናብኝ ከዚህ ዓለመ ሥጋ አሰናብተኝ ወደዘለዓለማዊ ሕይወት አሣውረኝ በማለት የሕይወት ባለቤት ክርስቶስን ተማጸነ ። አቤቱ "ኢትመውት ዘእንበለ ትርዓይ መሢሐ ለእግዚአብሔር" ብለህ እንደተናገርከ በወገኖችህ ፊት ያዘጋጀኸውን አድኅኖትህን አይቻለሁና አሰናብተኝ። በማለት በተመስጦና በደስታ እየመሰገነ ለመነ ፣ ቀጥሎም የጌታን እናት ማርያም ሆይ! ይህ ሕፃን ፡

ለብዙዎች ለጥፋታቸው ፤ ለውድቀታቸው ፣ ለብዙዎች ደግሞ ለትንሣኤያቸው ፣ ለክብራቸው የተገለጠና የተዘጋጀ ነው ። ባንቺ ግን እንደሰይፍ የሚከፍል ኀዘን በልብሽ ያድራል በማለት ትንቢት ተናግሯል ። (ሉቃስ ምዕራፍ ፪ ቁጥር ፳፭-፴፭) ።

የስምዖን ትንቢት ደርሷል ፣ ተፈጽ



www.ethiopianorthodox.org

ሟል ፣ ጌታን ያልተከተሉትና የተቃወሙት ብዙዎች ተሰናክለዋል ፣ በስሙ ያመኑና የተከተሉት ልዕልና ነፍስን አግኝተዋል ። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም ወደግብፅ ከተሰደደችበት ጊዜ ጀምሮ ክርስቶስ በመስቀል እስከሞተበት ጊዜ ድረስ ልቡናዋን እንደጦር የሚወጋ ከባድ ኀዘን ደርሶባታል ። ስምዖን ካህን ፍጻሜው ያማረና የተወደደ አረጋዊ ነበር ። የዓለምን ቤዛ ለመታቀፍ መብቃቱ ሌላው ከፍተኛ ዕድል ነው ። በዚህ ዓለመ ሥጋ ብዙዎች ረጅም ዕድሜን ለማግኘት ፈጣሪያቸውን ይለምናሉ ፡ ዕድሜያቸው ቢረዝምም ምንም ቁም ነገር ሳይሠሩበት ያልፋሉ ። አረጋዊ ስምዖን በእግዚአብሔር ፈቃድ እስከ ጌታ ልደት ድረስ በዚህ ዓለም ሲቆይ ደግ ፣ ቅን ፣ ኃዳጌ በቀል ፣ መንፈስ ቅዱስ ያደረበት እንደነበር ተጽፎለታል ። በዘመናችን ሽማግሌዎች ያስፈልጉናል ታዲያ ነገር የሚያውጠነጥኑ ፡ እንዱን ካንዱ የሚያጣሉ ነገርን ገማቾችና ፈታዮች ሳይሆኑ የተጣላ አስታራቂዎች በጸሎታቸው በረከትን ከእግዚአብሔር የሚያስጡ እንዲሆኑ ያስፈልጋል ። በምክራቸው ፣ በፍቅራቸው ለወጣቶች አርአያ የሚሆኑ አረጋውያን የሌላት ሀገር ታላቅ ውድቀት ይደርስባታል ። "ረድኤት ፣ በረከት ያለው ሽማግሌ አያሳጣን" የሚባለውም ስለዚህ ነው ። እንደስምዖን ያለ ደግ ፣ ቅን ፣ ኃዳጌ በቀል መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሽማግሌ እያሳጣን ።

ሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ገ/ሥላሴ

# የነበር ይናገር

የፋሽስት እንደራሴ የነበረው ግራዚያኒ የካቲት ፲፪ ፲፱፻፳፱ ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ሕዝብ ላይ የፈጸመው የሞት እልቂት ሦስት ምክንያት እንደነበረው አዋቂዎች ገምተውታል ። አንደኛ በአድዋ ጦርነት የኢትዮጵያ ጀግኖች ድል በማግኘታቸው የሞቱትን የወገኖቹን ደም ለመበቀልና ኋላ ድል በመሆናቸው ብድር ለመመለስ ሲሆን ሁለተኛ አውሮፓ መንግሥታት አፍሪካን እንደዳቦ እየቆራረሱ የሚከፋፈሉበት ወቅት በመሆኑ ለፋሽስቶችም ኢትዮጵያ ደርሳቸው ስለነበር በየሰበቡ ህዝቡን ጨርሶ መሬቷን ለመረከብ ሦስተኛ በዚያን ዘመን በኢጣሊያ መንግሥት ላይ ታላቅ ኪሳራ ደርሶበት ህዝቡ ደህይቶና ሥራ አጥ ሆኖ ስለነበር ሽብር አስነስቶ የኢትዮጵያን ሃብት ለመዝረፍና ዋና ዋናውን የንግድ ቦታ ለመያዝ የታቀደ ዘዴ ነበር ።

ይህም በመሆኑ የአዲስ አበባን ከተማ ዙሪያ በሽኾማ ሽቦ አጥሮ አራት በር ብቻ አበጅቶ ይህ የነጭ ሰፈር ነው ይህ የጥቁር መንደር ነው በማለት ህዝቡን ያሰቃየውና ያስቸግረው ጀመር ። የፋሽስት መሪ ይህንን ሲል አያስገርምም በመስኮት ዘሎ የገባ ሌባ ወንበዴ እንጂ በበሩ የገባ ቸር ጠባቂ አይደለምና የመጣውም ከአውሬ ለመጠበቅ ሳይሆን እራሱ አውሬ ስለሆነ ሊያርድ ሊገል ፣ ሊያጠፋ ነው የመጣው በጎቹ እንዲረቡ እንዲበዙ ሳይሆን እንዲያልቁ ህይወትን ለመስጠት ሳይሆን እንዲሞቱ ስለሆነ ምንደኛ ነው ።

ይህንንም ተግባር መጀመሪያ በአቡነ ጴጥሮስ ላይ ገልጦ አሳየ አቡነ ጴጥሮስንም የገደለበት ምክንያት አቡነ ጴጴጥሮስ ከሞቱ ሕዝቡ ሁሉ ፈርቶ ስለሚገዛ አገሩ ሰላም ይሆናል ። በማለት ነበር እሳቸውም ሲሞቱ መሬቷ እንዳትገዛለት አውግዘው ስለነበር የህዝቡ ቁጣ ገንፈለ በሀገሪቱም ላይ ሰላም እየጠፋ ይሄድ ጀመር ።

ሁኔታው በዚህ ላይ እንዳለ የካቲት ፲፪ ፳፱ ዓ.ም. በዓል የሚከበርበት ቀን ደረሰ የሰፈር ሹማምንትንም በየሰፈሩ እየተዘዋወሩ ህዝቡ በሰልፍ በዓሉን እንዲያከብር ከሰልፍ የቀረ ግን እርምጃ የሚወስድበት መሆኑን ሲለፍፉ ሰነበቱ የቤተ ክህነትም ሹማምንት ቀደም ብሎ ትዕዛዙ ደርሶአቸው ስለነበር የአድባራትና የገዳማት አለቆች የየቤተ ክርስቲያኑ ሹማምንት የማዕረግ ልብሳቸውን እየለበሱ ካህናቶቻቸውን ይዘው እንዲገኙ ትዕዛዝ ተላለፈላቸው እኔም የቅድስት ሥላሴ ደብተራ ሆኜ በቶፍነት አገልጋይ ስለነበርኩ ከጓደኞቼ ካህናት ጋር አብሬ ሄጄ ነበር ።

በዓሉም የሚከበርበት ሥፍራ ቀድሞ የላይኛው ቤተመንግሥት የነበረው አሁን ግን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እየተባለ የሚጠራው ነው እንደተባለውም ህዝቡ ተሰብስቦ ተሰለፈ ያን ጊዜ ከወንዶች በስተቀር ሴቶች አይሰለፉም ነበር ። መርዝ የተቀላቀለበት የሞት ሥጦታ ነው ።

የካህናቱ ለዘብ እንዳለቀ በኦሮምኛ በአማርኛ በትግሪኛ የሚተረጉሙ ሦስት አስተርጓሚዎች ቀረቡ ግራዚያኒም በድምጽ ማጉያ ይፎክር ጀመር ወዲያው የቦምብ ፍንዳታ ድምጽ ተሰማ ህዝቡም ሽሽት ጀመረ እኔንም መሪዬ ይዞኝ ሸሸ ሦስት ቀን ሙሉ ቃጠሎና ተኩስ ሲካሄድ ሰነበተ አብያተ ክርስቲያናትም ሳይጸለይባቸው ሳይቀደስባቸው ለሦስት ቀን ያህል ተዘጉ ፋሽስቶች የአራዳ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያንን በቦምብ መቱት የቅዱስ ጊዮርጊስንም ታቦት አጋፋሪ በየነ ይዘውት የሄዱት ያን ጊዜ ነው ።

የነበረ ይናገር የሚለውን ከተገነዘባችሁልኝ ያየ ይናገር የሚለውን ደግሞ የሀንጋሪው ዶክተር ላዳሲስ ሻባ የቀዶጥገና ሐኪም የነበሩት ያን ጊዜ ያዩትን ለፓንክረስት የሚከተለውን ተናግረው ከነበሩት ፍሬ ነገሩን ላንባቢ እናቀርባለን "ከቀኑ ፭ ሰዓት ሲሆን ግራዚያኒ ከከጄኔራሎቹ ጋር የክብር ስፍራውን ያዘ ንግግር እንደጀመረ ከሁለት ወጣቶች ሁለት ቦንብ ፈነዳ እሱና ተከታዮቹ ከጠረጴዛው ሥር ደንግጠው ተደፉ ሌላ ቦንብ እንደማይወድቅ በተረዱ ጊዜ ከመካከላቸው አንድ የፋሽሽት ጄኔራል ሽጉጥ ተኮሰ ቀጥሎ ከረምኀሪዎች ጥቁር ለባሽ ወታደሮች ተኩስ ከፈቱ ከ፫፻ በላይ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያኖች ገደሉ ።

ደካሞችንም የቆሰሉትንም ጨረስዋቸው በግቢው የሚገኘውን ሰው ሁሉ ገድለው ከጨረሱ በኋላ እየተሯሯጡ ወደ ከተማው ገቡ ያገኙትንም ይጨፈጭፉት ጀመር ከአንድ ሰዓት በኋላሱቆች ሁሉ እንዲዘጉ ተደረገ ። ይህንን ስቃይ ኤምባሲዎች እንዳያስተላልፉና በየከተማው ዳር ያሉትም አርበኞች ለእርዳታ እንዳይደርሱ ፖስታ ቤቶች ቴሌግራም ቴሌፎን እንዲዘጉ ታዘዘ የፎቶግራፍ ማንሻ ቤቶች ሁሉ ተዘጉ ከኢጣሊያ በስተቀር አንድ ሰው በየመንገዱ እንዳይዘዋወር ተከለከለ ። እንደ ክረምት ጐርፍ የህዝቡ ደም ሲፈስ የሬሳ ክምር በየስፍራው ተከምሮ አይቻለሁ ። ሲመሽም ሰውን በገዛ ቤቱ እየዘጉ በቤት ውስጥ አቃጠሉት ከተማውም ብርሃን ሆነ።

በዚህ ጊዜ ግራዚያኒ ባንድ ሐኪም ቤት ቆስሎ ይታከም ስለነበር በመስኮቱ የከተማውን ቃጠሎ እያየ ዳግማዊ ኔሮን ሆኖ በቃጠሎው ይስቅና ይደሰት ነበር ። ከደስታውም የተነሣ ግድያና ቃጠሎው ለሁለት ቀን እንዲቀጥል አዘዘ ። የፈሰሰውን የህዝቡን ደምና ሬሳ እያዩ ጣሊያኖች ሲዘፍኑና ሲደሰቱ አደሩ። በማግሥቱ የካቲት ፲፫ ቀን ፳፱ ዓ.ም. ራስ መኮንን ድልድይ እየገቡ ሲረሽኖአቸው አይቻለሁ ። የተማሩትን የሚገድሉበት ለሁለት ምክንያት ነበር አንደኛ የህዝቡን አስተሳሰብ ትምህርት እያስተማሩ እንዳይገዙ ያደርጋሉ ። እንዲሁም የተደረገውን ግፍ ወደ ውጭ ያስተላልፋሉ ። ሁለተኛ ውብና ድንቅ የሆኑ ዕቃዎችን ከአሮፕ አስመጥተው ከቤት ስለነበራቸው ይህንን ለመዝረፍ እንዲመቻቸው ነው ። በዚሁ ቀን የዘረፉትን ወርቅ እና ብር ለመመንዘርና ልዩ ልዩ ጌጥ ለመለወጥ የፋሽስት ወታደሮች የባንኩን በር አጣበውት ይታይ ነበር ።

እኔም ሐኪም እንደመሆኔ መጠን ብዙ የጣሊያን ሐኪሞች ከእኔ ጋር ይሰሩ ነበር ፣ ይህን ያህል ወርቅ ዘረፍኩ ይህን ያህል ብር ወሰድኩ እያሉ ከማውራታቸውም ሌላ አንዱ አምስት ብቻ ገድያለሁ ሲል ሌላው ደግሞ ከ፳ በላይ ገድያለሁ እያለ ሲናገር ሰምቻለሁ ።

ሌሎቹ ደግሞ ሬሳውን ሲሰበስቡ ተመልክቼአለሁ ለምሳሌ እኔ በአንደኛው የዓለም ጦርነት የጦር ሜዳ ሐኪም ሆኜ ብዙ ሰው ሲያልቅ አይቻለሁ ብዙ ሬሳም ተመልክቻለሁ ይህ ሁሉ ሲሆን ህይወቴን አልቀፈፈውም ልቤንም አላስደነገጠውም በህዳር በሽታም ጊዜ ብዙ ሰው ሲያልቅ ተመልክቻለሁ መቅሰፍት ስለሆነ ስሜቴን አለወጠውም በየካቲት ፲፪/፳፱ ዓ.ም. በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ፋሽስት የፈጸመው ግፍ ግን መሣሪያ በሌለው በሰላማዊ ሰው ላይ ስለሆነ ህሊናዬን እስከመሳትና አዕምሮዬን መቆጣጠር እስከ ማልችልበት ደረጃ ላይ ደርሻለሁ ሲሉ መስክረዋል።

ሐኪሙ እንደመሰከሩት ከመከራው ታላቅነት የተነሣ በርከት ያሉት ወገኖቻችን ቢያልቁም በብዙ እልፍ የሚቆጠሩ አርበኞችን ቀስቅሷል። የኢትዮጵያ ሰማዕታትም ደም የነፃነትና የክብር ፍሬ አፍርቶ ለሀገር አበርክቷል ። የፋሽስት መሪና ግብረ አበሮቹ ይህን የመሰለ እልቂት የፈጸሙት ፋሽዝምን በኢትዮጵያ ላይ ለማቋቋም ነበር ። በቤንዚን ላይ እሳት ሲጨመር ነበልባሉ እየበረከተ እንደሚሄድ ሁሉ ፋሽሽስት የኢትዮጵያን ህዝብ ሐይል አዳክማለሁ ብሎ ሲያቅድም የኢትዮጵያ ህዝብ ሐይል እየበረታ ከመሄድ በቀር አልደከመም በመጨረሻም ፋሽዝምና መሪዎቹ ሲደመሰሱ ኢትዮጵያ ነፃነቷን ባጭር ጊዜ ልታገኝ ችላለች ።

የፋሽዝምን ጨለማነትና ባርነት በህዝቡ ላይ የፈጸመውን ስቃይና ግፍ የኢትዮጵያ አርበኞች የፈጸሙትን ተጋድሎ ግን የካቲት ፲፪ አደባባይ የቆመው የመታሰቢያ ሐውልት በየጊዜው ለሚነሳው ትውልድ ሲመሰክር ይኖራል ። ጀግና ህዝብ በየጊዜው ታሪኩን ይደግማልና

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

# ልማት በቤት ክርስቲያን

በዚህ ባለንበት ምድራዊ ዓለም አሉ ከሚባሉት ዋና ዋና ሥራዎችና የሰውን ሕይወት ይጠብቃሉ ተብለው እምነት ከሚጣልባቸው ነገሮች መካከል አንነቱና የመ፟ጀመሪያውን ደረጃ ይዞ የሚገኘው ተግባረ እድ ነው ቢባል ትክክለኛና እውነተኛ መልስ ነው እንላለን ።

የሰው ሕይወት ተጠብቆ የሚኖረው በእህልና በውኃ መሆኑ ከማንም ሰው የተሠወረ አይደለም እንዲያውም ጠቢቡ ሲራክ ቀዳሜ ሕይወቱ ለሰብእ እክል ወማይ (የሰው ሕይወት እህልና ውኃ ናቸው ሲል የተናገረው ዓረፍተ ነገር ከዚህ የተነሣ ነበር ።

ይሁን እንጂ የሰው ሕይወት እህል ነው ስንልም እህል በቧልት በጨዋታ እጅና እግርን አጣምሮ ጀርን አቀርቅሮ ወሬ ሲያወሩ በመዋል ሳይሆን ተግቶና ነቅቶ ላብን እያንጠፈጠፉ በመሥራት ነው እንጂ ለእሥራኤል መና ከደመና ወርዶላቸው ነበርና ለእኔም መና ከደመና ይወርድልኛል በሚል አጉል ሐሳብ የሚገኝ አይደለም ።


ጥበብ(ተግባረዕድ) ለሚከተላት ሰው ሁሉ የሕይወት ዛፍ ስትሆን ለሚይዟትም የሰላምና የብርታት መቋሚያ ናት ይህንንም በመገንዘብ በአንዳንድ ታላላቅ አድባራት የተለያዩ ተግባራት እድ እየተካሄዱ ናቸው ። ቢሆንም በአሁኑ ጽሑፋችን የምናተኩረው በደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን ስለ ተቋቋመው የእደ ጥበባት ሥራና በዚሁ ቤተ ክርስቲያን ስለሚካሄደው የማሠልጠኛ ሥራ ነው በደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን ያለው የእደ ጥበብ ማሠልጠኛ እንዴት እንደ ተቋቋመና ማን እንዳቋቋመው የደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ መምህር ብርሃነ መስቀል ተፈራን አነጋግረናቸው ነበር ትንሣኤ ይህ በደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን የተቋቋመው የእደ ጥበብ ማሠልጠኛ በስንት ዓ/ም ነው ?

መልስ በዚህ በደብረ ናዝሬት የሚካሄደው የእደ ጥበባት ሥራ የተቋቋመው በ1976 ዓ/ም ነው ይሁን እንጂ በዚህ በተጠቀሰው ዓ/ም ቢቋቋምም በአንዳንድ ምክንያት ሥራውን ሊያካሂድ አልቻለም ነበር ሥራውን በሚገባ ማካሄድ የጀ፟ረው አሁን በ1977 ዓ/ም ነው ።

ትንሣኤ የእደ ጥበባትን ሥራ ያቋቋመው ማን ነው ?

እደ ጥበባት ማሠልጠኛ ተልከው ሲማሩ ቆይተው ሥራውን በሚገባ አውቀውና አጠናቅቀው የእውቀታቸውንም መመዘኛ የምሥክር ወረቀት ተቀብለው የመጡ ናቸው እነዚህ ካህናትና ዲያቆናት አሁን በደብረ ናዝሬት የሚገኙትን ካህናትንና ዲያቆናቱን እንዲሁም መዘምራንን ሲያሰለጥኑ ይገኛሉ ።

ትንሣኤ በደብረ ናዝሬት የእደ ጥበባት ሥራ መካሄዱና መቋቋሙ መልካም



የደብረ ናዝሬት ቅ. ዮሴፍ ካህናት በሽመና ሥራ ላይ

መልስ ሥራውን ያቋቋመው የደብሩ ሰበካ ጉባኤ ሲሆን የሰበካ ጉባኤው ከኪሱ ገንዘብ አውጥቶ ሳይሆን ከልዩ ልዩ ስለትና ስጦታዎች እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ከሚገኘውና ከአንዳንድ በጎ አድራጊዎች ምእመናን በተገኘው እርዳታ ነው ሊቋቋም የቻለው ።

ትንሣኤ የዚሁ የእደ ጥበባትን ሥራ የሚያካሂዱት እንዴት ያሉት ሰዎች ናቸው?

መልስ ፦ ሥራውን የሚያካሂዱትና ካህናቱን የሚያሰለጥኑት የደብሩ አገልጋዮችየሆኑ ካህናትና ዲያቆናት ናቸው። እነዚህም ቀደም ሲል ወደ ማዕከላዊ የ

ነው ነገር ግን ካህናቱ ዲያቆናቱና መዘምራኑ ከዚህ ከሰለጠኑ በኋላ ወዴት ይሄዳሉ የሚቀጥራቸውስ ማን ነው ?

መልስ ፦ በዚህ የእደ ጥበባት ማሠልጠኛ የሚሰለጥኑት ካህናትና ዲያቆናት የደብሩ አገልጋዮች እንደመሆናቸው መጠን ራሱ የዚሁ ሰበካ ጉባዔ ይቀጥራቸዋል ። እንጂ ወደ ሌላ የሚሄዱ ወይም ሌላ ሰው የሚወስዳቸው አይደሉም ምክንያቱም ይህ የእደ ጥበባት ማሠልጠኛ ሊቋቋም የቻለው ከዚሁ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ዲያቆናት በጠቅላላ አገልጋዮቹ ሁሉ ከዚሁ እየሰሩ እንዲሻሻሉና



ራሳቸውን በራሳቸው እየረዱ እንዲኖሩ ኑሯቸውንም እንዲያሻሽሉ የተቋቋመ እንጂ ለሌላ ነገር ስላልተቋቋመ ከዚህ ሰልጥነው ወደ ሌላ የሚሄዱ አይደሉም።

ይሁን እንጂ ከቤተ ክህነት ተልከው ለመሰልጠን ሊመጡ የወደዱም ቢኖሩ የመጡልንን ለማሰልጠን ዝግጁ ነን ይህ ማሠልጠኛ የእኛ ካህናትና ዲያቆናት የሚሰለጥኑበት እንጂ ሌሎችን አንቀበልም የምንልበት ምክንያት የለንም ወደ እኛ የመጣውን ለማሠልጠን ወደ ኋላ አንልም ።

ትንሣኤ ለመሆኑ ከተቋቋመ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ለሽያጭ የቀረበ የእጅ ሥራ አለወይ ?

መልስ ፦ አዎ ምንም እንኳ ሥራውን ከጀመረ ጥቂት ቀን ቢሆንም ከሱፍ ክር የተሠሩ የሴቶችና የወንዶች የተለያዩ የጥበብ ልብስንና እንዲሁም የጠረጴዛ ልብስ እንዲሁም ለሶፋ ወምበሮች ልብስ የሚያገለግሉ ልብሶች ሠርተን እንደ አቅማችን ለገበያ አቅርበን መሸጥ ጀምረናል ።

ትንሣኤ ከእደ ጥበባቱ ሽያጭ የተገኘውን ገቢ የሚቆጣጠረው ማን ነው?

መልስ፦ የሚሠራበት የሱፍ ክርንም ሆነ ሌሎች ዕቃዎችን ማንኛውንም የእደ ጥበባት የሚያገለግሉትን ሁሉ የሚያቀርብ የሰበካ ጉባዔው ስለሆነ ከሽያጭ የሚገኘውንም ገቢ የሚቆጣጠረው ያው ሰበካ ጉባዔ ነው ምክንያቱም ራሱ የሰበካ ጉባዔው ከሠለጠኑት ካህናት መካከል አንዱን መርጦ እየተከታተለ እንዲቆጣጠር መድቦአልና ትንሣኤ ለዚሁ የእደ ጥበባት ሥራ ከሚያገለግሉ ነገሮች ዋና ዋናዎቹን ቢገልጹልን ?

መምህር ብርሃነ መስቀል ተፈራ ለዚሁ ሥራ የሚያስፈልጉንና የምንጠቀምባቸው 1ኛ የሱፍ ክር

2ኛ/ የመኪና ክር

3ኛ/ ከድርና ከማግ የተሠሩ ክሮች ናቸው ። የምንጠቀመው በእነዚህ ለወንዶቹም ለሴቶችም የሚያገለግለውን ልብሰ እንሠራለን ።

ከዚህም ሌላ በሥጋጃ ሥራ (ሞያ) የሠለጠኑ ባሁኑ ጊዜ አነስተኛ የሆኑ ከቀጫ የሚሠሩ የእግር መጥረጊያ ምንጣፎችንና እነሱንም የመሳሰሉትን ተግባረዕድ በመሥራት ላይ ይገኛሉ ።



መ/ ብርሃነ መስቀል ተፈራ የደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ

እዎ መጀመር ሁሉም ይጀምራል ከፍጻሜ ማድረሱ ግን ብዙ መሥዋዕትነትን ይጠይቃል ። ስለዚህ ይህ የተጀመረው የእደ ጥበባት ሥራ የበለጠ ምርት ለማምረት እንዲበቃ ምኞታችን ነው ከእናተም በጋለ መንፈስ መሥራት ይፈለግባችኋል እንላለን ።

ከነፈርግብ ማርቆስ

---

## ደብዳቤዎች

ክፍ ፩ የዞረ

እንግዲህ ይህ ሁሉ ማስረጃ እያለ በዘመነ ብሉይ መላእክት ለተልእኮ አይወጡም አይወርዱም ነበር ማለት አይቻልም ።

፬ኛ/ ወደሀገረ በሳዕተ ሰብእ ሂዶ ያስተማረው ሐዋርያው ታዴዎስ ሳይሆን እንድርያስ ነው ። ሰው የሚበሉ የተባሉትም የግብራቸውን ስፋት ለመግለጽ የተሰጠ ቅጥል ነው እንጂ ሰውን ሰው የሚበላው ሆኖ አይደለም ። ነቢዩ ኢሳይያስ ፱.፳፩ ምናሴ ኤፍሬምን ኤፍሬም ምናሴን ይበላዋል እርሳቸውም በአንድ የይሁዳ ጠላት ናቸው ሲል ገልጾታል ። በዚህ ቃል መሠረት በቅዱስ መጽሐፍ ሰውን ሰው ይበላዋል ። የሚለው ቃል ገንዘብን ጉልበትን የሚመለከት ነው እንጂ ሰው ሰውን አይበላውም ።

፭ኛ/ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው በዕንጨት ላይ ሲሆን ቀሳውስት የብረት የናስ የብር የወርቅ መስቀል ለምን ይይዛሉ ስላልከው የዕንጨትም ሆነ የብረት የብርም ሆነ የወርቅ መስቀል ቀሳውስቱ የሚይዙት የጌታችን የመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስን መከራ መስቀል ለማስታወስ ነው ። መድኃኒታችን ስለእኛ ኃጢአትና በደል መሞቱን ማስታወሻ ከሆነ መስቀሉ የብረትም ሆነ የእንጨት የብርም ሆነ የወርቅ ልዩነት አይኖረውም ታላቁ ቁም ነገር ክርስቶስ ስለእኛ በደል ልዩ ልዩ መከራን ተቀብሎ መሞቱን ማመንና አለመዘንጋት ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

# ፕሮፌሰር ሐየርና ተከታዮቻቸው በሰሜን ኢትዮጵያ ጉብኝት አደረጉ

ፕሮፌሰር ሃየርና ተከታዮቻቸው ከአለፈው ህዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. እስከ ታህሣሥ ፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም በሰሜን ኢትዮጵያ በተለይም በጐጃምና በጐንደር ሀገረ ስብከቶች በአብነት ቦታዎች በገዳማትና በአብያተ ክርስቲያናት ጉብኝት አድርገዋል ።

እንግዶቹ በጐጃም ሀገረ ስብከት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሥር የሚገኙትን የዕጓለ ማውታ የሕፃናት ማሳደጊያ አዳሪ ቤቶችን ጐብኝተዋል ። ቡድኑ በደብረ ማርቆስ ከተማ አጠገብ የሚገኘውን የፈለገ አርዝ የሕፃናት ማሳደጊያ አዳሪ ቤት ለመጐብኘት ከቦታው በደረሱ ጊዜ እጅግ የደመቀ አቀባበል ተደርጐላቸዋል ። በዚህም ጊዜ በወጣቶችተዘጋጅቶ የቀረበው የ[illegible]ዳዊ ሽብሸባ እንግዶቹን ከመጠን በላይ አስደስቷቸዋል ። በፈለገ አርዝ መንፈሳዊ የሕፃናት ማሳደጊያ ት/ቤት ከ፸፬ ወጣቶች በላይ የሚገኙት ሲሆን ሁለገብ የሆኑ መንፈሳዊውንና ዘመናዊውን ትምህርት አጣምረው የያዙ ወጣቶች ይገኛሉ ።

ከፕሮግራሙ ፍጻሜ በኋላ ለእንግዶቹ የዕራት ግብዣ ተደርጐላቸዋል ። ቡድኑ በደብረ ማርቆስ ከተማ አዳር ካደረገ በኋላ በማግስቱ ጉዞውን ወደ ሞጣ በመቀጠል እግረ መንገዱን ከዋናው መንገድ ወጣ ብሎ የሚገኘውን የዲማ ጊዮርጊስን ቤተ ክርስቲያን ጐብኝቷል። ደብረ ዲማ ወደ ዐባይ ሸለቆ በምሥራቅ በኩል ገባ ብሎ የሚገኝ ታላቅ ደብር ሲሆን ቀደም ሲል በአፄ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት የተተከለ መሆኑ ይነገራል አፄ ዳዊትም ለዚህ ደብር ሲሶ መንግሥታቸውን ሰጥተው እንደ ነበር ይተረካል አፄ ዮሐንስ ብዙ ወርቅና ልብስ ዘውዳቸውን ጭምር እንደሰጡት በተጨማሪ ተረድተናል ። አቡነ ተክለ አልፋ ዘዲማ በዚህ አካባቢ ወንጌልን በመስበክ የክርስትናን ትምህርት በማስፋፋት በሕዝቡ ላይ ከባድ ችግር ትፈጥር የነበረችውን መውሊድ የተባለችውን ርኩስ መንፈስ ከሕዝቡ ላይ እንድትወገድ በማድረግ ከፍተኛ ሥራ ሠርተዋል ። ከዚህ በኋላ እንግዶቹ የጐበኙት የደብረ ወርቅን ገዳም ነበር በዚች ገዳም ውስጥ ፱፱ መነኮሳት የሚገኙ ሲሆን የሚተዳደሩትም በግብርና ሙያ ላይ ተሠማርተው ነው ።

ከዚህ በኋላ ጉዞ ወደ ሞጣ ከተማ በማድረግ በዚያ የሚገኘውን የሕፃናት ማሳደጊያ ት/ቤት ጐብኝተዋል ። በሞጣ የዕጓለ ማውታ የሕፃናት ማሳደጊያ ት/ ቤት ፳፩ ያህል ተማሮች ሲገኙ በቅርቡ ከኮረም የመጡ ፳፭ ሕፃናት ይገኛሉ እንግዶቹ ለነዚህ ሕፃናት የተለየ የገንዘብ ዕርዳታ አድርገውላቸዋል ። ህዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. እንግዶቹ ባህር ዳር ከተማ የሚገኘውን የአዳሪ ሕፃናትት/ቤት በመጐብኘት ተመሳሳይ ርዳታ አድርገዋል ። ፕሮፌሰሩ በዚህ ሕፃናት ማሳደጊያ ለሚገኙት ተማሪዎች በአደረጉት ንግግር እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል ።

"ይህ ት/ቤት የተሠራው በአምደ ጽዮን ዘመነ መንግሥት በተመሠረቱት ገዳማትና በዚህ በጣና ሐይቅ አካባቢ ከቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን አጠገብ በመሠራቱ እጅግ ደስ የሚያሰኝ ነው ። ካሉ በኋላ" እናንተ በዚህ ትምህርት ቤት የምትማሩ ተማሮች የጥንቱንና የአሁኑንትምህርት ለመማር ጥሩ ዕድል አላችሁ" ብለዋል ። ከዚህ በኋላ እንግዶቹ በባህር ዳር ግዮን ሆቴል ምሣ ከበሉ በኋላ ጉዞአቸውን ወደ ወረታ ከተማ በመቀጠል በዚያ የሚገኘውን የወረታ አዳሪ ቤት ጐብኝተዋል ። የወረታ አዳሪ ትምህርት ቤት ከከተማው ወጣ ብሎ ለትምህርት እጅግ አመቺ በሆነ ሥፍራ ላይ የተመሠረተ ከመሆኑም በላይ በተለይ ለግብርና ሙያ እጅግ ተስማሚ ነው ። የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ያላቸው በጣም ደስ የሚሉ ወጣቶች በብዛት ይገኙበታል ። እነርሱም በጥሩ ዝግጅት በያሬዳዊ ሽብሸባ ለእንግዶቹ ጥሩ አቀባበል አድርገውላቸዋል ። ከዚህ በኋላ እንግዶቹ ማምሻቸውን ተጉዘው ደብረ ታቦር ከተማ ሲደርሱ ከከተማዋ ወጣ ብለው የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ መርቆሬዎስና እንዲሁም እነፊታውራሪ አጥናፉ የደብረ ታቦር መንፈሳዊ አዳሪ ት/ቤት ተማሮችን በሰልፍ አሰልፈው የደመቀ አቀባበል አድርገውላቸዋል ።

በደብረ ታቦር አዳሪ ቤቱን ከጐበኙ በኋላ በዚያው አዳር ሆነ ። በጠቅላላው እንግዶቹ በየደረሱባቸው አዳሪ ቤቶች ውስጣዊ ድርጅታቸውንና ይዞታቸውን ከመመልከታቸውም በላይ በተለይም አዲስ ከኮረምና ቆቦ ለመጡት ሕፃናት የተለየ የገንዘብ ዕርዳታ አድርገውላቸዋል ። ከዚህ በኋላ እንግዶቹ ከደብረ ታቦር ከተማ በመነሳት በመጀመሪያ የጐበኙት በደብረ ታቦር አውራጃ በእስቴ ወረዳ ውስጥ የምትገኘውን አስደናቂዋን የማህደረ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ነበር ።

ጉዞአችንን ወደ ማህደረ ማርያም ቀጥለን ማህደረ ማርያም ደርሰን እጅግ አስደናቂ የሆነችውን የማህደረ ማርያምን ቤተ ክርስቲያን ሥዕሎች በተመለከትን ጊዜ በመንገድ ላይ ተሰምቶን የነበረውን ድካም ሁሉ ልንረሳው ችለናል ። ይህችን ቤተ ክርስቲያን አፄ ዮሐንስ በዘመነ መንግሥታቸው ዘዮሐንስ በተባለ ሠዓሊ እጅግ አሣምረው እንዳሣሏት ተረድተናል ። የዚህችንም ቤተ ክርስቲያን ሥዕሎች ዘዮሐንስ እጅግ አሳምሮ ከሣላት በኋላ አፄ ዮሐንስ ሌላ ቤተ ክርስቲያን እንዳይስል ከለከሉት ይባላል ።

በዚች ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያን ብዙ የጥንት የክብር ዕቃና ብዙ የታሪክ ቅርስ ይገኛል ። የነአፄ ዮሐንስ ዘውድ የነእቴጌ ጣይቱ የወርቅ ዋንጫ ከወርቅና ከብር የተሠሩ አልባሳት በብዛት ይገኙበታል ። ይህቺ ታሪካዊት ቤተ ክርስቲያን ለወደፊቱ መንገዷ በደንብ ከተሠራ ብዙ የሀገር ጐብኚዎችን የምትስብና ለሀገሪቱም ታላቅ የታሪክ ቅርስ የምትሆን ናት ።

ከማህደረ ማርያም መልስ እንግዶቹ የጐበኙት የእስቴ መካነ ኢየሱስን ገዳም ነበር ። እስቴ መካነ ኢየሱስ አመሠራረቱ ቀደም ሲል በጻድቁ ዮሐንስና ቀጥሎም በአድያም ሰገድ ኢያሱ ዘመናት ሲሆን በጠላት ዘመን ጠላት አቃጥሎት እንደነበረና ከጠላት በኋላ እንደተሠራ ይነገራል ።

የዚህ ገዳም ካህናት ቀደም ብለው ፕሮፌሰር ሐየርን ያውቁአቸው ስለነበረ ከዋናው መንገድ ድረስ በመውጣት በክበሮና በሽብሸባ ተቀበሉአቸው "በዚህ ገዳም ውስጥ ጥንታዊውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የሚያስተምሩ ሦስት መምህራን ይገኙበታል እነርሱም የመጻሕፍተ ትርጓሜ ፡ የቅኔ የድጓ መምህራን ናቸው ። ፕሮፌሰር ሐየር ከታቦር ሶሳይቲ ይዘውት የመጡትን የአንድ ዓመት ቀለባቸውን አንድ ሺህ ብር በቦታው ላይ ሲደርሱ ሰጥተዋል ። ከዚህ በኋላ ጉብኝቱ የቀጠለ የዙር አምባ ገዳምንና ቤተ ልሔምን ነበር ። ዙር አምባ ዙር አባ መንገለ ምሥራቅ ተብሎ የእግዚአብሔር መላክ የቋጥኙን መውጫ ለአባ አረጋዊ እንደነገራቸው ይተርካሉ ። ይህ ገዳም በአቡነ አረጋዊ ስም የሚጠራ ሲሆን ንጉሡ አፄ ገብረመስቀልና አባ አረጋዊ ከትግራይ መጥተው እንደመሠረቱትና በአሁኑ ጊዜ የአንድ ሺህ አራት መቶ ዘመን ታሪክ ያለው ቦታ መሆኑ ይነገራል ። በዚህ ቦታ ላይ ሊቁ ቅዱስ ያሬድም" ይሄው ጽዋ መላእክት በሰማያት አድከዋ አድከዋ ወርእኩ ሥነ ሕንጼሃ በማለት የዘመረበትን ተራራ ተመለከትን ። ይህን ገዳም ግራኝ አቃጥሎት እንደነበረና እንደገናም ኢያሱ አድያም ሰገድ መልሶ እንደሠራው ይነገራል ። በዚህ ገዳም ውስጥ ብዙ ታሪካዊ ቅርስና ጥንታዊ ሥዕል ይገኝበታል ። እንግዶቹ ዙርአምባን ከጐበኙ በኋላ ወደ ቤተልሔም በመጓዝ እጅግ ውጣ ውረድ የሆነውን የቤተ ልሔም መንገድ አቋርጠን ቤተ ልሔም ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ላይ ደረስን ። ቤተ ልሔም ቆላማ በሆነ ሥፍራ ከመንገድና ከመገናኛ እጅግ ዕርቃ የምትገኝ ቦታ ናት ። ይህች ቦታ እንዴት የድጓ ምስክር እንደሆነች ሲናገሩ እንዲህ ይላሉ ። በግራኝ ወረራ ምክንያት አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ሲቃጠሉ ድጓው አብሮ ስለጠፋና ከጊዜ በኋላ በዚች ቦታ ድጓው በመገኘቱ የምስክር ቦታ ልትሆን ችላለች" ይላሉ ። ቤተ ልሔም የጥንቱ ትምህርት እንደቀጠለ ይገኛል ። እጅግ ደስ የሚሉ የድጓ ተማሮች በብዛት ይገኙበታል ። በአሁኑ ጊዜ ግን ረሀብ ስለገባ ብዙዎቹ ለቀው እንደሄዱ ተረድተናል ። ፕሮፌሰር ሐየርም ከታቦር ሶሳይቲ ያመጡትን ሦስት ሺህ ብር የአንድ ዓመት ቀለባቸውን በዚህ ጊዜ አስረከበዋል ። በአጠቃላይ ዙርአምባም ሆነ ቤተ ልሔም የገንዘብ ዕርዳታ የሚያገኙት በጀርመን ሀገር በፕሮፌሰር ሐየር አማካይነት ከተቋቋመው ታቦር ሶሳይቲ እየተባለ ከሚጠራው ድርጅት ነው ። ከቤተ ልሔም መልስ ቡድኑ የጐበኘው የንፋስ መውጫን የዕጓለ ማውታ የሕፃናት ማሳደጊያ ት/ቤት ነው ። ከዚህ በኋላ እንግዶቹ በደብረ ታቦር ከተማ ቆይታ በማድረግ በደብረታቦር ከተማና አካባቢው የደብረ ታቦር ኢየሱስን እናቲቱ ማርያምንና ልጂቱ ማርያምን ጐብኝተዋል ። ቡድኑ በደብረ ታቦር አካባቢ ጉብኝቱን ካጠናቀቀ በኋላ ወደ ጐንደር በማምራት በዚያ የሚገኙትን ታሪካዊ ሥፍራዎችና አብያተ ክርስቲያናት ጐብኝተዋል በጐንደር ከተማ የደብረ ብርሃን ሥላሴን የፋሲልን መዋኛ ሥፍራ የሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ አዳሪ ቤትንና የዳባት ሕፃናትማሳደጊያ ት/ቤት ጐብኝተዋል ። ቡድኑ በጐንደርና በጐጃም ክፍላተ ሀገር የሚያደርገውን ጉብኝት በማጠናቀቅ ጉዞውን ወደ አዲስ አበባ በማምራት እግረ መንገዱንም የጠራ ገዳምንና ዐባይ ሸለቆውስጥ የሚገኘውን ዋሻ ሚካኤልን የደብረ ሊባኖስን ገዳም ጐብኝቷል ። ቡድኑ የዋሻ ሚካኤልን ገዳም በጐበኘበት ወቅት ይህ ዋሻ ጥንት አምልኮተ አሪት ይፈጸምበት እንደነበረና በኋላም ወደ አምልኮተ ሐዲስ በአብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት በጳጳሱ በአቡነ ሰላማ እንደተለወጠ ይነገራል ። ሁለቱ ወንድማማቾች አብርሃና አጽብሃ ከጳጳሱ ከአቡነ ሰላማ ጋር በባዩን ተሻግረው በዚህ ቦታ ከነሠራዊታቸው ካደሩ በኋላ ይህን ዋሻ ከአምልኮተ አሪት ወደ አምልኮተ ሐዲስ ለውጠው የቅዱስ ሚካኤልን ጽላት አስገብተው ቤተ ክርስቲያን እንዳደረጉት በገድሉ ላይ ተጽፎ ይገኛል ። ቡድኑ ከኅዳር ፳፱ ቀን እስከ ታህሣሥ ፺ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ድረስ ያደረገውን ጉብኝት አጠናቆ አዲስ አበባ በተመለሰበት ቀን ታኅሣሥ ፰ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ፓትርያርክ የራት ግብዣ አድርገውላቸዋል ። እንዲሁም የመታሰቢያ ስጦታ አድርገውላቸዋል ። ከዚህ በኋላ ቡድኑ በኢትዮጵያ የሚያደርገውን ጉብኝት ፈጽሞ ታኅሣሥ ፱ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ወደ ሀገሩ ተመልሷል ።

የዜናው አቅራቢ ከሃሊ አስፋው





www.ethiopianorthodox.org

# የግብርና በረከት

እግዚአብሔርም አለ እነሆ መብል ይሆናችሁ ዘንድ በመሬት ሁሉ ዝሩ በእርሱ ያለውንም ሐመልማል ሁሉ የዛፍን ፍሬ የሚያፈራውንና ዘር ያለውንም ዛፍ ሁሉ ሰጠኋችሁ ይላል አሪት ዘፍ. ም. 1 ቁ. ፳፱ በዛሬውም የግብርና በረከት የምናቀርብላችሁ ጽሑፍ ከግብርና ሚኒስቴር ከማስታወቂያና ከሕዝብ ግንኙነት ክፍል ግብርናችን በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ የሚለውን ይሆናል ።

መጽሔቱ ጽሑፉን ሲጀምር የተፈጥሮ ሃብት ሲባል ሰው ምንም ዓይነት ድካም ሳያደርግ በነፃ አግኝቶ የሚጠቀምባቸውን ሁሉ ያጠቃልላል ይልና ሐተታውን በማራዘም ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት አስፈላጊ የሆኑትን እንደ ዕፅዋት አፈርና ውሃ የመሳሰሉትን ይሆናል ። ዕፅዋትና እንስሳት ሕልውናቸውን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የመሰረቱት በአፈርና በውሃ ላይ ነው ።

የውሃ መባከንም ሆነ የአፈር መሸርሸር ምክንያት ሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ ነው የሁለቱም ህልውና በዕፅዋት የተደገፈ ስለሆነ ዕፅዋቱ ያለአግባብ እየተመነጠሩ በእሳት የሚጋዩ ከሆነ ድርቀት ይመጣል ውሃ አይገኝም አፈሩንም የሚደግፈው ኃይል ስለሌለ በነፋስ ኃይልም ሆነ በውሃ ማዕበል እየተጠረገ ይሄዳል መሬትም ንጥረ ነገሮችዋ በመጠረጉ የማበቀል ኃይሏ ይቀንሳል ።

ሰውና እንስሳት ለመኖር ሲሉ ከአካባቢያቸው ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት ወይም በአካባቢው ላይ የሚአደርጉት ተፅዕኖ የተፈጥሮ ሚዛን ከመጠን በላይ መናጋቱ በአየር ንብረት መለወጥ ይከሰታል ። አፈርን በነፋስ በውሃና በመሳሰሉት ከመሸርሸርና ከመጠረግ ማዳን እንደሚቻልም የአፈርና የውሃ ጥናት ሣይንስ ያስተምራል ይህውም ዕፅዋትን በመትከል እርሻን ለጐርፉ ናዳ እንዳያመች አድርጐ በአግድመት በማረስ ቦይ በመቆፈር ፡ እርከኖችንና ክትሮችን በመሥራት በጠቅላላው ዘመናዊና ሣይንሳዊ የመሬት አያያዝና አጠቃቀም ዘዴዎችን ተግባራዊ በማድረግ መከላከል ይቻላል ።

የኢትዮጵያ መልክዐ ምድር በተራሮች በኮረብታዎች በሜዳዎችና በሸለቆዎች የተከፋፈለ ሲሆን በአጠቃላይም ለምለምና በተፈጥሮ ሃብቷ የተደነቀች ቀደም ሲልም በደን የተሸፈነችና ልዩ ልዩ የዱር አራዊትና አዕዋፍ የሚገኙባት ሃገር እንደነበረች ታሪክ ይመሰክራል ሆኖም ከሀገሪቱ የተፈጥሮ አቀማመጥና ከዝናም አጣጣል መጠን የተነሣ የመሬት መሸርሸር በተለይ በተራራማው በከፍተኛ ቦታዎች ያጠቃልላል።

በአብዛኛው የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገር የነበረው የተፈጥሮ ደን ለእርሻ ፀረ ሰብል አራዊትን ለማስወገድና ለማገድ እንጨት እየተባለ ያለአግባብ እየተጨፈጨፈ በመቃጠሉ ሥርአት በሌለው የመሬት አጠቃቀም በመደረጉ ከጊዜ ወደ ጊዜ የዝናም የምንጮችና ጅረቶች መጠን መቀነስ ፡ የምርት ማሽቆልቆልና የዱር አራዊት መጥፋት ከጀመሩ ቆይቶአል ።

ሆኖም ኢትዮጵያ ይህን የተፈጥሮ ሃብት መባከንን ጉዳይ ዝም ብላ አልተመለከተችም የተፈጥሮ ደንን መጠበቅ አስፈላጊነት ከአጤ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ይታሰብበት ስለነበር የደኑ መራቆት የዝናም ማጣትና ድርቅን የሚያስከትል መሆኑን በማሰብ በወቅቱ ዛፎች እንዳይቆረጡ የሚያግዱ አንዳንድ ደንቦች ወጥተው እንደነበር ታሪኩ ይናገራል ።

ሆኖም እንደማንኛውም ታዳጊ ሀገሮች የሀገራችን የእርሻ ሥራ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ በመሆኑና ለመሬት ተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ምንም ዓይነት እንክብካቤና ጥንቃቄ ያልተደረገለት ስለነበር የተፈጥሮ ልባሱ የነበሩት ዕፅዋት ተገፈው አፈሩ ታጥቦ ለነፋስና ለፀሐይ የተጋለጠ ስለሆነ የተፈጥሮ ልምላሜን በየጊዜው እያጣች መምጣቷ የታወቀ ነው ። ይህም የተፈጥሮ መናጋት ሊፈጠር የቻለው ከመሬት አጠቃቀምና ቁጥጥር የተነሣ መሆኑ ይታወቃል በሌላ በኩል የአፈርና ውሃ ጥበቃን በሚመለከት አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ኑሮ በግብርና ላይ የተመሠረተ እንደመሆኑ መጠን ገበሬውን በማስተማር አስፈላጊውን መከላከል ያደርግ ዘንድ ማስተማር ያስፈልጋል ስለአፈር አያያዝና አጠቃቀም ለምሳሌ ዘመናዊ የአስተራረስ ስልቶችን የሰብል ማፈራረቅ ዘዴዎችን ፡ የአፈርና የድንጋይ ግድብና የክትር ሥራዎችን ፡ የዛፍና የሌሎችም ዕፅዋት ተከላ ማስፋፋትን በገጠር በገበሬው መካከል በሰፊው በማካሔድ በገጸ ምድር ውሃ ልማት በኩልም የአፈር ግድብ፡ የምንጭ ማጐልመስ የኩሬ ቁፋሮ ወዘተ ተግባራትን በማስፋፋት ለጐርፍ መቆጣጠሪያ ብቻ ሳይሆን ገበሬው ለመስኖ ለመጠጥ እንዲጠቀምበት ለማድረግ ከአለፉት ዓመታት ልምድ በመነሣት በተበታተነና ባልተቀነባበረ መልክ የነበረው አሰራር ተለውጦ የተፋሰሰ ልማት ሥራ በአንዳንድ ክፍላተ ሀገር እንዲቀጥል ተደርጓል ። እንዲሁም አፈርን ለመጠበቅ የሚያስችሉ በእርሻ መሬቶች የጐርፍ መቆጣጠሪያ ወይም መግቻ እንደ ክትሮች እርከኖች የመሳሰሉትን ሳይንሳዊ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴዎችበማድረግአፈሩበውሃና በነፋስኃይልእንዳይወሰድ ዕፀዋቱበእንስሳትከሚገባበላይእንዳይጋጡና መሬት እንዳይጋለጥመከላከሉበየቦታው ያለም ክንያት የሚባክነው የገጸ ምድር ውሃ እመች በሆነ ቦታ ተጠራቅሞ ለልማት እንዲውል ፡ የአነስተኛ ወንዞች ጠለፋ እንዲደረግ ፡ ኩሬዎችን በመቆፈር ከሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ።

የአፈር መበላትን ወይም መሸርሸርን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ዕፀዋት በርከኖች በቦዮችና ክትሮች እየተተከሉ አስፈላጊውን አገልግሎት እንዲሰጡ የማድረጉን አጠቃቀም ገበሬው እንዲለምደው የመቀስቀሱ የማስተማሩና የማስተባበሩ ተግባር መካሔድ አለበት ።

ስለዚህ የሁላችንንም ሕይወት የተመሠረተው በአፈር በውሃ በዕፀዋት ላይ ስለሆነ ይህ ሥራ እገሌን ይመለከታል ይህ ሥራ የእነገሌ ነው እኔን ምን አገባኝ ሳንል ሁላችንም በዛፉ ተከላ በክትር ሥራ ቦይ በመገደቡ ተግባር ተሳታፊ መሆን ይፈለግብናል ማን ነው በራሱ ሕይወት የሚለግም ማን ነው ለራሱ ኑሮ ደንታ የሌለው እንግዲህ ይህ ከሆነ ድር ቢያአብር አንበሳ ያስር ነውና ሁላችንም ተባብረን መነሳት አለብን ።

ፍሥሐ ባንቲ



# የጤና ዓምድ

## ፫. የሕፃን አስተዳደግ

ካለፈው የቀጠለ

፩ኛ/ የሕፃኑ ንፅሕና፦ የሕፃኑ ልብሶችና ሰውነቱ በየጊዜው መታጠብ አለባቸው በተለይ የሽንት ጨርቆቹን በጥንቃቄና በንጽሕና መያዝ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም በሽንት ሙቀትና መቆጥቆጥ የተነሳ ሰውነቱ ሊላጥና ሽፍታ ሊያወጣ ስለሚችል ነው ። ከዚህም ሌላ የሽንት ጨርቆች በየጊዜው በደንብ ካልታጠቡ ሕፃኑን ነጭ ናጫና ብስጩ ያደርጉታል ። ከዚህም በላይ የሕፃኑ እትብትና እምብርት በሚገባ በንጽሕና መያዝ መታጠብና በለስላሳ ጨርቅ ማድረቅ ያስፈልጋል ። ወዲያው ደርቆ ካልዳነ ወደ ሀኪም ወስዶ ማሳየቱ ጠቃሚ ነው ። የንጽሕና አጠባበቁና አያያዙ ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚያስፈልግ ሳይሆን እስከ ሚያድግ ድረስና ከዚያም በኋላ መቀጠል አለበት የግል ንጽሕናው ብቻ ሳይሆን የአካባቢና የቤተሰብ ንፅሕናው ሁሉ በሚገባ መጠበቅ አለበት ይህም በጣም አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች ዋነኛው ነው ።

፪ኛ/ የሕፃን አመጋገብ

አንድ ሕፃን ከተፀነሰ ጀምሮ ምግብ ያስፈልገዋል ሆኖም የአመጋገቡ ሁኔታ ከዕድሜው ጋር የሚመጣጠን መሆን አለበት ።

ከተወለደ ጀምሮ አራት ወር ባለው ጊዜ የእናቱን ጡት ብቻ መጥባት አለበት ቀደም ብለን እንደጠቀስነው በተለያዩ ምክንያቶች እናት ልጅዋን ጡት መከልከል የለባትም ጡቱ ደርቋል እንበ. አለኝ በማሉ ምክንያቶች ሕፃን ጡት መከልከል ለብዙ አደጋዎች ሊያጋልጡት ይችላሉ ።

ከአራት ወር በኋላ ሕፃኑ ጡትም እየጠባ ተጨማሪ ምግብ እንደ አጃ አጥሚት የፍራፍሬ ጭማቂ ተቀቅሎ የተፈጨ ድንች የተቀቀለ ዕንቁላል በወተት እያለሰለሱ በማስጀመር ቀስ በቀስ ማለማመድ ያስፈልጋል። ሕፃን የለመደው ጡት ስለሆነ አዳዲስ ምግቦች ሲቀርቡለት ለመጀመሪያ ጊዜ እንቢ እያለ ቢያስቸግርም በትእግሥት በመከተል እንዲለምድ ማድረግ ያስፈልጋል ።

ከስድስት ወር በኋላ እንጀራ በአልጫ ሽሮ ወይም መረቅ ፈትፍቶ ማብላት በርበሬ ቅመም ከሌለው የአዋቂ ምግብ አለስልሶ ማብላት ይጠቅማል ፡ ሆኖም ሕፃኑ ታዳጊ እንደመሆኑ መጠን የሚመገበው ምግብ የተመጣጠነ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል ይህም ማለት ከእህል ዘር ከጥራጥሬ ከአትክልትና ከፍራፍሬ ከሥጋ ከዕንቁላል ከወተትና ዓሣ የተወጣጣ ምግብ መመገብ ያስፈልገዋል ።

ሕፃኑ አንድ ዓመት ሲሞላውም ጥርስ ስለሚያወጣ የአዋቂዎችን ምግብ በደንብ ሊለማመድ ይችላል በማንኛውም ጊዜ የሕፃኑ ምግብ በንጽሕና መዘጋጀትና መመገብ አለበት ውሃም ከሕፃንነቱ ጀምሮ ቀስ በቀስ ትንሽ ትንሽ እየለማመዱ ማጠጣት ያስፈልጋል ። በኢትዮጵያ ለብዙ ሕፃናት መታመምና መሞት ምክንያት የሆነው የምግብ ማነስና አለመመጣጠን በመሆኑ የሕፃናትን አመጋገብ በደንብ በጥንቃቄ መከታተል ያስፈልጋል ።

ለሕፃናት የፀሐይ ሙቀት አስፈላጊነት

አንድ ሕፃን ተወልዶ ከሁለተኛ ሳምንት በኋላ በየቀኑ ጠዋት ለግማሽ ሰዓት እራቁቱን አድርጎ ፀሐይ ማሞቅ ያስፈልጋል ። ይህም ለአጥንቱ ዕድገትና ጥንካሬ አስፈላጊ ነው ስለዚህ ሪኬትስ ( የአጥንት መልፈስፈስ) በሽታን መከላከል ይቻላል ።

፫ኛ/ ሕፃናትን ከበሽታ መከላከል

ሕፃናት ለማንኛውም ዓይነት በሽታ ከሁሉም ሰው በላይ የተጋለጡ ናቸው ። ስለዚህ ከፍተኛ ጥንቃቄና እንክብካቤ ያስፈልጋቸዋል ።

ንፅሕናን በመጠበቅ ከልዩ ልዩ የቆዳ በሽታዎች ሌላም ተላላፊ በሽታዎች ለመጠበቅ ይችላል ። እንዲሁም የአካባቢን ንጽሕና በሚገባ በመጠበቅ ከልዩ ልዩ ተቅማጦች የአንጀት ትሎችና የመሳሰሉት በሽታዎች መጠበቅ ስለሚችሉ የንጽሕናን አጠባበቅ በሚገባ መከታተል ጠቃሚ ነው ።

-የተመጣጠነ ምግብ መመገብም ሰውነትን በሚገባ ገንብቶና አጠንክሮ በበሽታ በቀላሉ ከመጠቃት ሊከላከል ስለሚያስችል ሕፃናት ለሰውነታቸው ዕድገትና ከበሽታም ለመጠበቅ የተመጣጠነ ምግብ መመገብ አለባቸው ።

-ሕፃናትን ከበሽተኞች ማግለልና በተቻለ መጠን ሕፃናት በሽተኞችን እን



www.ethiopianorthodox.org

ዳይጠት ማድረግ ይጠቅማል ። በተለይ ተላላፊ በሽታ የቆየ ሳል ያለባቸው ሰዎች ከሕፃናት ቢርቁ መልካም ነው በተጨማሪም አዋቂዎች በሽተኞችን ለመጠየቅ ሲሄዱ ሕፃናትን ይዘው ወይም አስከትለው መሔድ የለባቸውም ።

-ክትባት ከልዩ ልዩ በሽታዎች ሊከላከሉ የሚችሉ የተለያዩ ክትባቶች አሉ እነዚህም ክትባቶች በተለያዩ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚሰጡ ስለሆነ የሕፃኑን ዕድሜ በመጠበቅ ማስከተቡ በጣም ጠቃሚ ነው ።

ነቀርሳ መከላከያ

-ሁለት ወር ሲሞላው ጀምሮ የትክትክ የመንጋጋ ቆልፍና የዘጊ አነዳ መከላከያና እንዲሁም የሕፃንነት ልምሻ በሽታ መከላከያ ክትባት ሊወሰድ ይገባል።

እነዚህን ክትባቶች አንድ ጊዜ ብቻ መውሰድ በቂ ሊሆን ስለማይችል ለሦስት ጊዜ በየወሩ በማከታተል መውሰድ በጣም ጠቃሚ ነው ።

-የኩፍኝ በሽታ መከላከያ ክትባት ሕፃኑ በተወለደ በዘጠነኛ ወሩ መውሰድ ያስፈልጋል ።

ኩፍኝ በተለይ በኢትዮጵያ የብዙ ሕፃናት ሕይወት መጥፊያ ከሆኑት ምክንያቶች አንዱ በመሆኑ የኩፍኝ መከላከያ ክትባት ሕፃኑን በወቅቱ ማስከተብ በጣም አስፈላጊ ነው ።

ስለዚህ ክትባቶች እጅግ በጣም ጠቃሚዎችና አስፈላጊዎች ስለሆኑ ሕፃናትን ወቅቱን ተከትሎ ማስከተቡ የማንኛውም ቤተሰብ ከባድ ኃላፊነት ነው ክትባቶች ልዩ ጥንቃቄ የሚያስፈልጋቸው መድኀኒቶች በመሆናቸው ሊገኙ የሚችሉት በጤና ድርጅት ብቻ ስለሆነ በአቅራቢያ የሚገኘውን የጤና ድርጅት መጠየቅ ተገቢ ነው ።

ሲስተር የሽወርቅ ከበደ

# ኪዳነ ምሕረት

ኪዳን ማለት የመተማመኛ ውልና የማይበጠስ የሰላም ገመድ ነው ሁለት ባልንጀሮች በጽኑ ፍቅር ተያይዘው በሚኖሩበት ወቅት እንዳይካካዱና በአንዳንድ ምክንያት ተጣልተው እንዳይለያዩ ሲሉ ይማማላሉ በዚህም በተማማሉበት መሠረት ፍቅራቸውን አጽንተው ይኖራሉ ፡ እንደዚሁም ሁሉ ሁለት ሦስት ሰዎች በአንዳንድ ነገሮች ተጣልተው በክፉ ነገር ሲፈላለጉ ይኖራሉ ። ነገር ግን የእነሱን ጠብና የእነሱን ጥላቻ ያወቁ ሽማግሌዎች አንተም ተው አንተም ተው በማለት በሁለቱ ጠበኞች የነበረውን ጥላቻ አስወግደው ያስታርቋቸዋል ። እነዚህ ሰዎች ከታረቁ በኋላ በመካከላቸው የነበረው ጥላቻ እንደገና እንዳያገረሽና በጠብ እንዳይፈላለጉ ቃል ኪዳን ይገባሉ ፡ ይማማላሉ ።

እንግዲህ ኪዳን የሚለው ቃልና መሐላ የሚለው አነጋገር በንባብ ይለያዩ እንጂ ትርጉማቸው አንድ ነው ልዩነት የለውም መሐላ ማለት ኪዳን ነው ኪዳን ማለትም መሐላ ነው ።

ከዚህ ላይ በርእሱ ኪዳነ ምሕረት ተብሎ የተጠቀሰው ለእመቤታችን የተሰጠ ቃል ኪዳን ማለታችን ነው የመጀመሪያው ሰው በበደለው በደልና በሠራው ኃጢአት እግዚአብሔርን አሳዘነው ከዚህም የተነሣ መልአኩን ልኮ ከተዋበችው ምድረ ገነት አስወጥቶ አባረረው በእግዚአብሔርና በአዳም መካከል የነበረውም መንፈሳዊ ግንኙነት ተቋረጠ ቢሆንም ለጊዜው ቢቋረጥ አዳም በበደለው በደል ጸንቶ ሊኖር አልቻለም ተጸጸተ ፈጣሪዬን አሳዝኛለሁ በማለት ለብዙ ዘመናት ሳያቋርጥ እንባውን እያፈሰሰ ቀንና ሌሊትም እያለቀሰ ከፈጣሪው ይቅርታን ጠየቀ እግዚአብሔርም ቸር ፡ ይቅር ባይ እንደመሆኑ እንደ በደለኝ ልበድለው ከእኔም በገዛ ስህተቱ እንደተለየ ይቅር ሳይል ያንተን እንባ በእውነት አይቻለሁ ፡ ልቅሶህንም ሰምቻለሁ አሁንም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ የሚል እውነተኛ ተስፋ ፡ ሰጠው ይህንንም ተስፋ በሰጠው አንዲት ደቂቃ እንኳን ሳያሳልፍ በአምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍስዋ ነፍስን ነሥቶ ባሕርይዋን ተዋህዶ ከተወለደ በኋላ በ30 ዓመቱ በመስቀል ተሰቅሎ የተለያዩትንም ጸዋተወ መከራ ተቀብሎ አዳነው ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ ተብሎ የተነገረው ተስፋ ፍጻሜ አገኘ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ይህንን መሠረት አድርጎ ሲናገር (ወእመ በጽሐ ዕድሜሁ ዘእስፋው እግዚአብሔር ፈነወ ወልዶ ወተወልደ እምብእሴት) እግዚአብሔር ለአዳም የሰጠው ተስፋ በደረሰ ጊዜ ተቀዳሚ ተከታይ የሌለው የባሕርይ ልጁን ላከ ከእመቤታችንም ተወለደ ብሏል ገላ. ፬፥፬ ።

እንግዲህ ተስፋ (ቃል ኪዳን) የተጀመረው በዚህ ጊዜ መሆኑን እንገነዘባለን እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ፲ ወር ከአምስት ቀን የተሸከመችውን በማሳሰብ እንዲሁም ራሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚያስተምርበት ወቅት ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ አንድጽዋ ቀዝቃዛ ውሀ ብቻ በደቀ መዛሙርት ስም ቢያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም ሲል ያስተማረውን በመገንዘብ በስምዋ ቀዝቃዛ ውኃ የሚያጠጣውን ቁራሽ እንጀራ ቆርሶ ለተራበው የሚያጎርሰውን እንዲምርላት በለመነችው ጊዜ ልመናዋን ተቀብሎ የምሕረት ኪዳን ሰጥቷታል

ስለዚህ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የካቲት ፲፮ ቀን እመቤታችን የምሕረት ቃል ኪዳን የተቀበለችበት ቀን በመሆኑ በያመቱ ስታከብረው ትኖራለች ።

ከነፈ ርግብ ማርቆስ





# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዛመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቲፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ስባት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፣

የስልክ ቁ. 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 1[illegible]
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org